# የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 935/2015

# A DIRECTIVE TO PROVIDE FOR COMMERCIAL REGISTRATION, LICENSING AND POST-LICENSING INSPECTION, NO. 935/2022

| | |
|---|---|
| **መግቢያ** | **Preamble** |
| የሕግና የአሠራር ክፍተቶችን በመድፈንና እርካታን በማሳደግ የንግዱ ማኅበረሰብ እና ኅብረተሰቡ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **Whereas**, it has become necessary to let the business community and the society play its part in the country's overall economic development by closing loopholes in the law and practices, and increasing satisfaction; |
| የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ወጭ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ለመረጃ አያያዝ እና ለንግድ ሥራ አመቺ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤ | **Whereas**, it has become necessary to create a conducive environment for doing business by providing cost effective, efficient, and accessible commercial registration and business licensing service with the support of modern technology and efficient data management; |
| በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ እና በድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሥራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለው አፈጻጸም ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ | **Whereas**, it has become necessary to establish a uniform practice of commercial registration and business licensing as well as post licensing inspection across the nation; |
| የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (በአዋጅ ቁጥር 1150/2011 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 | Therefore, this Directive is issued pursuant to Sub-article (2) of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 980/2016(as amended with proclamation |

የማስፈጸሚያ ድንጋጌ አንቀጽ 5 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 935/2015“ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) “**የንግድ ሕግ**“ ማለት የኢፌዴሪ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ነው፤
2) “**አዋጅ**“ ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (በአዋጅ ቁጥር 1150/2011 እንደተሻሻለ) ነው፤
3) “**ደንብ**“ ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009 (በደንብ ቁጥር 461/2012 እንደተሻሻለ) ነው፤
4) “**ሚኒስቴር**“ ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤
5) “**ኃላፊነታቸው የተወሰነ የንግድ ማኅበራት**“ ማለት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር፣ የአክስዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ እና ባለ አንድ አባል

1150/2017) and Article 5 of the Preface of the Commercial Code.

## PART ONE
## GENERAL PROVISION

**1. Short Title**

This Directive may be cited as“Commercial registration, Licensing and Post Licensing Inspection Directive No. 935/2022.“

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Directive;

1) “**Commercial Code**“ means Commercial Code of Ethiopia Proclamation No. 1243/2021;
2) “**Proclamation**“ means the Commercial registration and Business Licensing Proclamation No. 980/2016 (as amended by Proclamation No. 1150/2019);
3) “**Regulation**“ means the Commercial registration and Business Licensing Council of Ministers Regulation No. 392/2017 (as amended);
4) “**Ministry**“ means the Ministry of Trade and Regional Integration
5) “**Limited liability business organizations**“ means limited liability partnership, share company, private limited company and one-member private limited company;
6) “**Private limited companies**“ means private limited company and one-member private

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ነው፤

6) **"ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት"** ማለት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እና ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ነው፤
7) በአዋጁ አንቀጽ 2 የተደነገጉት የቃላት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዋጁ፣ በንግድ ሕጉ እና በደንቡ በተሸፈኑ የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና የኢንስፔክሽን ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## የድርጅት ስም እና የንግድ ስም ስለመመዝገብ፣ ስለመለወጥ፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

**4. የግለሰብ ነጋዴ የድርጅት ስም ስለመመዝገብ**

1) ማንኛውም የግለሰብ ነጋዴ የድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I በተዘጋጀው ቅጽ 01 የማመልከቻ ቅጽ ላይ የድርጅት ስም እንዲሞላ ይደረጋል።
2) የተጠየቀው አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 14 (1) የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ የንግድ ድርጅት ስሙን ከሚኒስቴሩ

limited company;

7) Definitions of words provided for in Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Directive.

**3. Scope of Application**

This Directive shall be applicable on commercial registration, business licensing and inspection matters covered by the Proclamation, Commercial Code and the Regulation.

## PART TWO
## REGISTRATION, AMENDMENT, SUBSTITUTE AND CANCELLATION OF BUSINESS NAME AND TRADE NAME

**4. Registration of Business Name of a Sole Proprietor**

1) Where a sole proprietor requests a service for registration of business name, the request shall be submitted by filling out the application Form 01 of Annex I attached to this Directive and submit same;
2) The name shall be registered by verifying it against the central commercial registration data base of the Ministry as provided in the Proclamation, provided that the requested service fulfills requirements indicated in Article 14/1/ of the Proclamation

**5. Registration of Business Name of a Business Organization**

1) Where a business organization requests a service for registration of business

| | |
|---|---|
| ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል። <br><br> **5. የንግድ ማኅበር የድርጅት ስም ስለመመዝገብ** <br><br> 1) ማንኛውም የንግድ ማኅበር የድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል። <br><br> 2) የተጠየቀው አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 14 (2)፣ (3)፣ (4)፣ (5) እና በደንቡ አንቀጽ 4 (1) እና (2) የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ የድርጅት ስም ምዝገባ በማጣራት ከሚኒስቴሩ ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ውስጥ በዚህ መመሪያ አባሪ III ስለድርጅት ስም በተመለከተው ማብራሪያ መሠረት ይከናወናል። <br><br> 3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተጣርቶ የተመዘገበው የድርጅት ስም የማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲጸድቅ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኝ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው | name, a request shall be submitted by filling out the application Form 01 of Annex I attached to this Directive with at least three alternative business names; <br><br> 2) Provided that the application fulfills the requirements indicated under Article 14 (2), (3), (4), (5) of the Proclamation and Article 4 (1) and (2) of the Regulation, verification of buisness name shall be conducted against the central commercial registration data base of the Ministry as provided in the explanation attached to this Directive as Annex III regarding business name; <br><br> 3) A letter shall be issued to the relevant bodies authorized by law to authenticate documents to cause the memorandum of association be authenticated, and to relevant tax authority to cause tax identification number (TIN) be issued in the business name verified in accordance with sub-Article 2 of this Article; or, as the case may be, the applicant will be availed of such service with the support of information communication technology without issuing letters. <br><br> 4) The business name issued in accordance with sub-Article 2 of this Article shall be registered with the registering body within six months as of |

አካል በደብዳቤ ይሸኛል፤ ወይም በደብዳቤ መሸኘት ሳያስፈልግ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ይደረጋል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተጣርቶ የተሰጠውው የድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በሚመለከታቸው አካላት መመሥረቻ ጽሑፉ ፀድቆ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወጥቶለት ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ በንግድ ምዝገባ መመዝገብ አለበት።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተጣራው የድርጅት ስም የማይመዘገብ ሆኖ ከተገኘ መዝጋቢው አካል የማይመዘገብበትን ምክንያት ገልፆ አመልካቹ ከጠየቀ ወዲያውኑ በጽሑፍ ያሳውቃል።

6) የኅብረት ሽርክና ማኅበራት እና ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለባቸው የሽርክና ማኅበራት የአባላቱን ስም ወይም ቢያንስ የሁለት አባላቱን ስም ወይንም ከአባላቱ ሥሞች በምህጻረ ቃል የተውጣጣ በድርጅት ስምነት የሚጠቀሙ ይሆናል። ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለባቸው የሽርክና ማኅበራትን በተመለከተ

the issuance of such business name upon authentication of the memorandum of association and issuance of tax identification number by the relevant bodies;

5) If the business name verified in accordance with sub-Article 2 of this Article is not eligible for registration, the registering body shall immediately notify the applicant, and in writing if requested by the applicant, by stating the reasons thereof.

6) General partnerships and limited partnerships shall use the names of the partners or at least two of its partners or an acronym taken from the names of the partners as their business name. In relation to limited partnerships, the business name shall contain the names, or acronyms of the names, of at least two partners with unlimited liability.

7) The name of limited liability partnerships to be submitted for registration shall reflect the purpose for which they are established;

8) Share companies, private limited companies and one-member private limited companies shall use a novel name;

9) The registration of a business name in

| | |
|---|---|
| ቢያንስ ሁለቱ ኃላፊነታቸው ያልተወሰነ አባላት ስም መሆን አለበት። | accordance with Article 15 (1) of the Proclamation shall be conducted at the place where commercial registration is carried out; |
| 7) ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማኅበራት የሚያስመዘግቡት ስም የተቋቋሙበትን ዓላማ የሚገልጽ መሆን አለበት። | |
| 8) የአክሲዮን ማኅበራት፣ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት እና ባለ አንድ አባል ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የፈጠራ ስም መጠቀም አለባቸው። | |
| 9) በአዋጁ አንቀጽ 15 (1) መሠረት የሚደረግ የድርጅት ስም ምዝገባ የንግድ ምዝገባ በሚያደርግበት ቦታ መመዝገብ አለበት። | |
| 10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት ተመዝግበው የተሰጡ የድርጅት ስሞች የንግድ ምዝገባ ከሚያደርጉበት ቦታ ምዝገባቸውን መውሰድ ይችላሉ። | 10) Without prejudice to the stipulation of sub-Article 9 of this Article, a business name registered in accordance with this Directive may be collected from the place where commercial registration is carried out; |
| 11) በአደራጆች በመቋቋም ላይ ያለ አክሲዮን ማኅበር የንግድ ምዝገባ ማመልከቻ በአደራጆች ሰብሳቢ ወይም በሥራ አስኪያጁ የሚቀርብ ሆኖ፣ አክሲዮን ማኅበሩ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት፣ አደራጆች ለአደራጅነት ብቁ ስለመሆናቸው ከሚኒስቴሩ ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ | 11) An application for registration of a share company under formation by promoters shall be submitted by the chairperson of the promoters or the general manager; provided however, promoters shall submit, to the registering body, a support letter, issued by the Ministry of Trade and Regional Integration or by the relevant body authorized by law to administer trade in regional states, testifying that they are competent to be promoters; |
| | 12) The registering body, upon receiving the application for registration, shall temporally approve the name after conducting verification of the proposed business names, business objective, number of shares, address, place of registration and other necessary items and require promoters to bring a support letter which indicates that they |

ሥልጣን ከተሰጠው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ምዝገባውን ለሚያከናውነው አካል ማቅረብ አለባቸው።

12) መዝጋቢው አካል የምዝገባ ማመልከቻው እንደቀረበለት ረቂቅ የድርጅት ስሞችን፣ የንግድ ዓላማውን፣ የአክሲዮን መጠን፣ አድራሻ፣ ምዝገባ የሚከናወንበትን ቦታ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማጣራቶችን አድርጎ ስሙን በጊዜያዊነት ካጸደቀ በኋላ፣ አደራጆቹ አክሲዮን ማኅበር ለማደራጀት ብቁ ስለመሆናቸው የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ፣ በጊዜያዊነት የጸደቀውን ስሙን፣ የንግድ ዓላማውን፣ እና የሁሉንም አደራጆች ሙሉ ስም ከነአድራሻቸው በመጥቀስ ወደ ሚኒስቴሩ ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት ይልካቸዋል።

13) ሚኒስቴሩ ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 249 መሠረት አመልካቾች ለአደራጅነት ብቁ መሆናቸውን አጣርቶ፣ አመልካቾች የጠየቁትን የንግድ ምዝገባ ለሚያከናውነው አካል በጊዜያዊነት የጸደቀውን ስሙን፣ የንግድ ዓላማውን፣

are qualified to act as promoters of share company and send a letter to the Ministry of Trade and Regional integration or the concerned body authorized by law with the power to administer trade in the region that indicates the provisionally approved name, objective of the business and full name of the promoters with their addresses;

13) The Ministry or the relevant body authorized by law with the power to administer trade in regions shall, after verifying the competency of the promoters in accordance with Article 249 of the Commercial Code, issue a support letter to the registering body indicating the provisionally approved name, objective of the business, full name of the promoters with their addresses and other necessary information;

14) The registering body shall, upon submission of the appropriate support letter by the promoters, issue letters to banks to open a blocked account in the name of the share company under formation in which the proceeds of sale of shares will be deposited and to bodies authorized by law to authenticate memorandum of

የሁሉንም አደራጆች ሙሉ ስም ከነአድራሻቸው እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመጥቀስ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል።

14) አደራጆች ተገቢውን የድጋፍ ደብዳቤ ለመዝጋቢው አካል እንዳቀረቡ፣ መዝጋቢው አካል የሥራ አስኪያጁን ወይም የአደራጆችን ሰብሳቢ ሙሉ ስም፣ የታደሰ መታወቂያ እና የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ እና ሌሎች ሰነዶችን እንዲያሟላ በማድረግ የአክሲዮን ማኅበሩን የድርጅት ስም በቋሚነት ካጸደቀ በኋላ፣ የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ገቢ የሚደረግበት ዝግ የባንክ ሒሳብ በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር የድርጅት ስም እንዲከፈት ለባንኮች፣ እንዲሁም የማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እንዲጸድቅ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኝ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በደብዳቤ ይሸኛል፤ ወይም በደብዳቤ መሸኘት ሳያስፈልግ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል።

15) የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ገቢ የሚደረገው በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር የድርጅት ስም

association and issue tax identification number upon final approval of the business name of the share company after submission of the full name of the general manager and chairperson of the promoters, renewed identification card, passport size photograph and other documents or provide the same with the support of information communication technology without issuing letters;

15) The proceeds of sale of shares shall only be deposited in a blocked bank accounts opened in the name of the share company under formation. The blocked accounts shall only be activated after the formation process, including formation audit, is completed and the company is put under the control of the shareholders and an authorization is given by the concerned body to activate the blocked account;

16) Promoters may open bank account in their names for operating costs or expenses.

## 6. Change of Business Name of a Business Organization

በሚከፈቱ ዝግ የባንክ ሒሳቦች ብቻ ይሆናል። እነኝህ በሚቋቋመው የአክሲዮን ማኅበር የድርጅት ስም የሚከፈቱ ዝግ የባንክ ሒሳቦች ሲንቀሳቀሱ የሚችሉት ማኅበሩ የምሥረታ ኦዲትን ጨምሮ ሁሉንም የምሥረታ ሂደት ጨርሶና ማኅበሩን ለባለአክሲዮኖቹ ካስረከበ በኋላ ከሚመለከተው አካል ሒሳቦችን ማንቀሳቀስ ይቻላል የሚል ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው።

16) አደራጆች ለሥራ ማስኪያጃ የሚጠቀሙበት የባንክ ሒሳብ በስማቸው መክፈት ይችላሉ።

**6. የንግድ ማኅበር የድርጅት ስም ስለመለወጥ**

1. ማንኛውም የንግድ ማኅበር የድርጅት ስም ለመለወጥ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የንግድ ማኅበራት የድርጅት ስም ምዝገባ ከሚኒስቴሩ ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት በዚህ መመሪያ አባሪ III ስለድርጅት ስም በተመለከተው ማብራሪያ መሠረት ይከናወናል።
3. ለመለወጥ የተዘጋጀው ያልጸደቀ ቃለ ጉባኤ ለመዝጋቢው አካል እንዲቀርብ ተደርጎ በማጣራት እንዲጸድቅ ሰነድን

1) Where a business organization requests a service for registration of business name, a request shall be submitted by filling out the application Form 01 of Annex attached to this Directive with at least three alternative business names and submit same;
2) the name shall be registered upon verification against the central commercial registration data base of the Ministry of Trade and Regional Integration; the verification shall be conducted as provided in the explanation provided for in Annex III attached to this Directive concerning business name;
3) a letter shall, upon submission of the unauthenticated minutes prepared for change of name, be issued to the body authorized by law to authenticate document and amend tax identification number or provide such service with the support of information communication technology;
4) the changed name shall be registered upon presentation of the minutes authenticated by a body authorized by law and a letter which shows the agreement of the tax office to a request made for a change of name and registration of the same;
5) the changed business name shall be

ስማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያሻሽል በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት በደብዳቤ ይሸኛል ወይም በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎቱ እንዲሰጥ ይደረጋል።

4. ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ ቃለ ጉባኤ እና የድርጅቱ ስም ተለውጦ እንዲመዘገብ ከግብር አስከፋዩ መሥሪያ ቤት የስምምነት ደብዳቤ ይዞ ሲቀርብ የተለወጠው የድርጅት ስም ይመዘገባል።
5. የተለወጠው የድርጅት ስም እና አድራሻ በሚኒስቴሩ ድረ ገጽ ይፋ ይደረጋል።
6. የተለወጠው የድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፀድቆ ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ ካልተመዘገበ የቀድሞው የድርጅት ስም እንደተለወጠ አይቆጠርም።

**7. የንግድ ስምን ስለመመዝገብ**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 5 እና በዚህ መመሪያ

publicized by posting on the website of the Ministry;

6) the changed business name shall not be deemed to have been changed if such change is not authenticated by a body authorized by law and is registered by the registering body within two months as of the date of issuance of the changed name.

**7. Registration of Trade Name**

1) Where a trader requests a service for registration of business name, a request shall be submitted by filling out the application Form 01 of Annex I attached to this Directive with at least three alternative trade names and submit the same;
2) The trade name shall be registered upon verification against the central commercial registration data base of the Ministry as per the requirements provided for in Article 5 of the Regulation and this Directive; the verification shall be conducted as per the explanation provided for in Annex III attached to this Directive concerning trade names;
3) A trade name registration certificate attached as Form 03 of Annex II shall be issued after verifying based on article of this article that the name is not held by another trader;

የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ የንግድ ስም ምዝገባ ከሚኒስቴሩ ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት በዚህ መመሪያ አባሪ III ስለንግድ ስም በተመለከተው ማብራሪያ መሠረት ይከናወናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተመዘገበው የንግድ ስም በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመሰጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባለመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም ቀይሮ እንዲያወጣ ይደረጋል።
5. በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ በሌሎች ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መደቦች ላይ የንግድ ስም ምዝገባ ሲጠየቅ አገልግሎቱን የሚያገኙት የንግድ ሥራ ፈቃድ መሰጠቱን አረጋግጦ የንግድ ምዝገባ ባደረጉበት ቦታ ይሆናል።

4) Where it is found that the verified business name has been issued to another trader by mistake or for any other reason and a complaint has been lodged to that effect, the trader shall be required to change his business name and the previous trader who took the name shall keep his entitlement;
5) Where a request is made for registration of business name falling within the category of businesses for which business licenses are to be issued by other sectoral offices in accordance with Article 21 sub article 4 of the Proclamation, the service shall be provided upon verification at the place where commercial registration took place;
6) Where a trader requests for registration of business name as a memorial, evidence showing the consent of heirs, shall be required to be produced.

**8. Change of Trade Name**

1) Where a trader requests a service for change of trade name registration, a request for change of name shall be submitted by filling out the application Form 01 of Annex I attached to this Directive with at least three optional business names and submit the same;
2) The trade name shall be verified against the central commercial registration data

6. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም በመታሰቢያነት እንዲመዘገብ ሲጠይቅ በመታሰቢያነት እንዲጠቀምበት በወራሾች ስምምነትን ያገኘ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

**8. የንግድ ስምን ስለመለወጥ**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ ስመለወጥ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢያንስ ሦስት አማራጭ የንግድ ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ የንግድ ስም ምዝገባ ከሚኒስቴሩ ማዕከላዊ የንግድ ምዝገባ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት በዚህ መመሪያ አባሪ III ስለንግድ ስም በተመለከተው ማብራሪያ መሠረት ይከናወናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የተሰወጠው የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተመዘገበው የንግድ ስም

base of the Ministry of Trade and Regional Integration as per the requirements provided for in Article 7 of the Regulation and this Directive; the verification shall be conducted as per the explanation provided for in Annex III attached to this Directive concerning trade name;

3) A trade name registration certificate shall be issued as prescribed in Form 03 of Annex II attached this Directive after verifying based on sub article 2 of this Article that the name is not held by another trader;

4) Where it is found that the verified trade name based on sub article 2 of this Article has been issued to another trader by mistake or for any reason and a complaint has been lodged to that effect, the trader shall be required to change his business name and the previous trader who took the name shall keep his entitlement;

5) The changed trade name shall be posted on the website of the Ministry.

**9. Substitute Trade Name**

1) Where a trader requests a service for substitute of trade name, a request for substitute of trade name shall be submitted by filling out Form 01 of Annex I attached to this Directive;

በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ስሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመሰጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባስመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም እንዲያወጣ ይደረጋል።

5. የተሰወጠው የንግድ ስም በሚኒስቴሩ ድረ ገጽ የንግድ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል።

**9. ምትክ የንግድ ስም**

1. ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ስም አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ ስም ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 03 መሠረት ምትክ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

**10. የንግድ ስም ስረዛ**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ

2) a substitute trade name registration certificate shall be issued as prescribed in Form 03 of Annex II attached to this Directive in accordance with requirements provided in Article 6 of the Regulation and this Directive;
3) without prejudice to Sub-article 1 of this Article, when the service is provided online, the customer may directly obtain a substitute trade name from the online system.

**10. Cancellation of a Trade Name**

1) Where a trader requests a service for cancellation of business name, a request for cancellation of business name shall be submitted by filling out Form 01 of Annex I attached to this Directive;
2) Evidence of cancellation shall be provided by cancelling the business name as requested if the requested service is fulfilled the requirements of article 8 of the regulation.

## PART THREE
## ISSUANCE, AMENDMENT, SUBSTITUTE AND CANCELLATION OF COMMERCIAL REGISTRATION

**11. Commercial Registration Certificate**

A commercial registration certificate of national application shall be prepared in working language and in English.

**12. Commercial Registration of a Sole Proprietor**

መመሪያ አባሪ I ቅጽ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ስም ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።

2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 8 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ የተጠየቀውን የንግድ ስም በመሰረዝ የስረዛ ማስረጃ ይሰጣል።

## ክፍል ሦስት
## የንግድ ምዝገባ ስለ መመዝገብ ስለማሻሻል፣ ስለ ምትክ እና ስለስረዛ

**11. የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት**

አገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በሥራ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

**12. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ**

1. ማንኛውም ግለሰብ ነጋዴየንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያአባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 9 መሠረት መስፈርቶችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት የንግድ

1) Where an individual trader requests a service for commercial registration, a request for commercial registration shall be submitted by filling out Form 02 of Annex I attached to this Directive;
2) A commercial registration certificate shall be issued as prescribed in Form 01 of Annex II attached to this Directive in accordance with requirements provided for in article 9 of the Regulation;
3) Where a business organization is found to be part of the property of a minor or judicially interdicted person, the tutor shall present the decision of the court which allows him to continue the business as evidence;
4) The amount of capital stated in Form 02 of Annex I filled out by the sole proprietor to acquire the service for issuance of Certificate of commercial registration shall be registered as capital of the sole proprietor.

**13. Commercial Registration of Business organization**

1) Where a business organization requests a service for commercial registration, a request for commercial registration shall be submitted by filling out Form 02 of Annex 2 attached to this Directive;
2) Without prejudice to the minimum capital provided for in the Commercial Code and

ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. አካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ሐብት ውስጥ እና በፍርድ የተከለከለ ሰው ሃብት ውስጥ የንግድ ድርጅት የተገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ የንግድ ድርጅቱን ሥራ እንዲቀጥል በፍርድ ቤት የተወሰነበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት።
4. የግለሰብ ነጋዴ ካፒታል የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት በሞላው አባሪ I ቅጽ 02 ላይ የመዘገበው የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል።

**13. የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ**

1. ማንኛውም የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. በንግድ ሕጉ የተቀመጠው ዝቅተኛ ዋና ገንዘብ መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ማኅበራት በመመሥረቻ / በመግለጫ ጽሑፎቻቸው ላይ የመዘገቡት የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል፤ ሆኖም የአክስዮን ማኅበር እና ኃላፊነታቸው የተወሰነ

the amount of money to be deposited in the blacked account for share company and private limited companies, the amount of capital stated in the memorandum of association or prospectus shall be registered as capital of the business company;

3) The establishment of the business organization in accordance with Article 7 (2) of the Proclamation shall be posted in the website of the Ministry with its name and address;

4) Where a business organization is found to be part of the property of a minor or judicially interdicted person, the tutor shall present the decision of the court which allows him to continue the business as evidence;

5) A commercial registration certificate shall be issued as prescribed in Form 01 of Annex II attached to this directive if the requested service fulfills the requirements provided for in article 10 or 11 of the Regulation;

6) It shall be ascertained that members of a limited liability partnership who makes contribution in the form of skill have valid

የግል ማኅበራት በንግድ ሕጉ የተቀመጠው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን እና በዝግ ሂሳብ የሚያሳዩት መጠን የተጠበቀ ነው።

3. በአዋጁ አንቀጽ 7 (2) መሠረት የንግድ ማኅበር ስለመቋቋሙ በሚኒስቴሩ ድረ ገጽ የድርጅቱ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል።
4. አካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ሐብት ውስጥ እና በፍርድ የተከለከለ ሰው ሃብት ውስጥ ባለአንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የንግድ ድርጅት የተገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ የንግድ ድርጅቱን ሥራ እንዲቀጥል በፍርድ ቤት የተወሰነበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት።
5. የተጠየቀው አገልግሎት እንደጥያቄው አይነት በደንቡ አንቀጽ 10 ወይም 11 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
6. ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ሙያተኞች የሆኑ አባላቱ የሙያ ምስክር ወረቀት ለመስጠት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የጸና የሙያ ማረጋገጫ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሌላ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና

professional competence certificates issued by a body authorized by law, or in the case of another limited liability partnership with legal personality, it possesses a valid certificate of competence to provide professional services similar or related to the business organization under formation;

7) A one-member private limited company shall submit the unilateral declaration of the member and an authenticated certificate of trust issued by a body authorized by law; in addition, the provisions concerning private limited company shall also be applicable;

8) where the applicant who requests a registration service is a share company formed by public prescription, it shall submit an audit report examined by an external auditor.

## 14. Amendment of Commercial Registration

1) Where a trader requests a service for amendment of commercial registration, a request for amendment of commercial registration shall be submitted by filling out Form 02 Annex I attached to this Directive;
2) An amended commercial registration

| | |
|---|---|
| ማኅበር ከሆነ ከሚመሠረተው ማኅበር ጋር ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ የሆነ የሙያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጸና የሙያ ፈቃድ ያለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት። | certificate shall, where the requested amendment is approved in accordance with requirements provided for in article 18 of the Regulation, be issued by posting on the website, where the service for amendment is accessible online; or, in places where online service is not available, by requiring the trader to return the original certificate of commercial registration; |
| 7. ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ማኅበሩን የሚመሰርትበት መግለጫ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የንብረት ጠባቂነት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለዚህም ያገለግላሉ። | 3) Where the business organization makes a capital amendment and the capital amendment is made in cash, the applicant shall submit the document on which the money is registered in the name of the members and a minute registered in the name of each member by a body authorized by law to authenticate document; |
| 8. የምዝገባ አገልግሎት የጠየቀው ለህዝብ ክፍት የሆነ የአክስዮን ማኅበር ከሆነ በውጭ ኦዲተር የተመረመረበትን የምሥረታ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት። | 4) Where a business organization makes a capital amendment and the capital amendment is in kind, a document which shows the agreement of the members and minutes authenticated by the body authorized by law shall be submitted; |
| 14. የንግድ ምዝገባን ስለማሻሻል<br>1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።<br>2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 18 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ | 5) Where a business organization makes a capital amendment and the capital amendment is made from dividends, a document verified by an audit report showing the existence of a recorded profit |

አገልግሎቶች በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ማሻሻያው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት የተሻሻለ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በጥሬ ገንዘብ በሚሆንበት ጊዜ ገንዘቡ በአባላቱ የተመዘገበበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል በእያንዳንዳቸው ስም የተመዘገበ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት።
4. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በዓይነት በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት።
5. የንግድ ማኅበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው ከትርፍ ክፍፍል

and agreed by all members and a minute authenticated by a body authorized by law shall be submitted;

6) In order to reduce the capital of a share company, a private limited company or a one-member private limited company, a proof endorsed by an authenticated minute which shows the reason given by the auditor for the reduction of the capital and the decision of the general meeting on methods of reduction shall submitted;
7) A capital reduction made in accordance with Sub-article 6 of this Article shall be registered if no objection is filed within one month as of the publishing of such reduction in a widely circulated newspaper.

**15. Issuance of Substitute Certificate of Commercial Registration**

1) Where a trader requests a service for substitute of certificate of commercial registration, a request for substitute of certificate of commercial registration shall be submitted by filling out Form 02 of Annex I attached to this Directive;
2) Where the request for substitute of certificate of commercial registration is approved as per the requirement provided in article 19 of the Regulation, a substitute certificate of commercial

የሚደረግ ከሆነ ማኅበሩ ያስመዘገበው ትርፍ ስለመኖሩ በኦዲት ሪፖርት ሳይ ተረጋግጦ በአባላቱ ጠቅላላ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት።

6. በንግድ ሕጉ መሠረት የአክስዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ እና ባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የካፒታል ቅነሳ ለማድረግ ኦዲተሮች ዋና ገንዘቡን መቀነስ ያስፈለገበትን ምክንያት እና በአቀናነሱ ሁኔታ ሳይ ለጠቅላላ ጉባኤው ማቅረባቸውን እና በጉባኤው የተወሰነበትን የሚያሳይ ማስረጃ በቃለ ጉባኤ ፀድቆ መቅረብ አለበት።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የሚደረግ የካፒታል ቅነሳ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ወጥቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ ቅነሳው ይመዘገባል።

## 15. ምትክ የንግድ ምዝገባ ስለመስጠት

1. ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ሳይ ምትክ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን

registration shall be issued as prescribed in Form 01 of Annex II attached to this Directive;

3) Without prejudice to Sub-article 1 of this Article, when the service is provided online, the customer may directly obtain a substitute commercial registration certificate from the online system.

## 16. Cancellation of Commercial Registration

1) Where a trader requests for service of cancellation of commercial registration a request for cancellation of commercial registration shall be submitted by filling out Form 02 of Annex I attached to this Directive;
2) Where a commercial registration of a limited liability business organization is canceled, the cancellation shall be posted on the system where online service is available after having ascertained the fulfillment of the requirements by a liquidator appointed by members in accordance with article 21 of the Regulation or where online service is not available, the trader shall be issued with the letter of cancellation of commercial registration by returning the original certificate of commercial registration;
3) When a commercial registration is cancelled, the registering body shall

እንዲሞላ ይደረጋል።

2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 19 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሠረት ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

**16. የንግድ ምዝገባ ስረዛ**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ አባላቱ በሰየሙት ሒሣብ አጣሪና በደንቡ አንቀጽ 21 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ስረዛው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ

notify the cancellation to the requesting party by a letter through the appointed liquidator;

4) Cancellation of commercial registration made in accordance with Article 11 (7) of the Proclamation shall take place after one month the date of publication of the notice of cancellation in a widely circulated newspaper at the expense of the applicant.

**17. Commercial Registration of Foreign Investor Engaged in Mining Sector**

Without prejudice to the requirements, with the exception contractual agreement, applicable to foreign business organizations engaged in the mining sector by winning international bids, the investor shall also submit a letter of support from a body authorized by law to regulate the sector.

## PART FOUR

## ISSUANCE, RENEWAL, AMENDMENT, SUBSTITUTE AND CANCELLATION OF BUSINESS LICENSE

**18. Issuance of Business License**

1) Where a trader requests a service for issuance of business license, a request for issuance of business license shall be submitted by filling out Form 03 of Annex I attached to this Directive;

| | |
|---|---|
| ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡<br>3. ማንኛውም የንግድ ምዝገባ ስረዛ ሲከናወን መዝጋቢው አካል ስረዛውን ስጠየቀው አካል በተሰየመው የሒሳብ አጣሪ በኩል በደብዳቤ ይገልፃል፡፡<br>4. በአዋጁ አንቀጽ 11 (7) መሠረት የንግድ ማኅበራት ምዝገባ ስረዛ የሚጸናው የስረዛው ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከአንድ ወር በኋላ መሆኑ ተረጋግጦ አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡<br>**17. በማዕድን ዘርፍ የሚሰማራ የውጭ አገር ነጋዴ የንግድ ምዝገባ**<br>በማዕድን ዘርፍ የተሰማራ የውጭ ሀገር ነጋዴ የንግድ ምዝገባን በተመለከተ በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው ስሚገቡ የውጭ ሀገር ድርጅቶች የተቀመጠው መስፈርት (ከውል ስምምነት ሰነድ በስተቀር) የሚያገለግል ሆኖ በተጨማሪ ማዕድንን ስማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አስበት፡፡<br>**<u>ክፍል አራት</u>**<br>**የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት፣** | 2) Where the request for issuance of business license is approved in accordance with article 23 to 26 of the Regulation, a business license shall be issued as prescribed in Form 02 of Annex II attached to this directive;<br>3) Where a foreign investor who is engaged in business by winning international bid wins another international bid, he has the obligation to obtain additional business license;<br>4) Without prejudice to the requirements applicable to other traders, where a trader who wants to engage in the transport sector requests for business license, the motor vehicle ownership certificate /Libre/ shall also be submitted.<br>**19. Renewal of Business License**<br>1) Where a trader requests a service for renewal of business license, a request for renewal of business license shall be submitted by filling out Form 03 of Annex I attached to this Directive;<br>2) Where the requirements are fulfilled as provided in article 30 of the Regulations, a renewed certificate of business license shall be issued as |

**ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ**

**18. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት እንደጥያቄው አይነት በደንቡ ከአንቀጽ 23 እስከ 26 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
3. በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚገባ ነጋዴ በጨረታ አሸናፊ ከሆነበት የንግድ ሥራ በተጨማሪ ሌላ ጨረታ ያሸነፈ ከሆነ ላሸነፈበት ጨረታ ተጨማሪ የንግድ ሥራ ፈቃድ የማውጣት ግዴታ አለበት።
4. በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ ለሌሎች ነጋዴዎች የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በተጨማሪ የተሽከርካሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ/ሊብሬ/ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

**19. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማደስ**

prescribed in Form 02 of Annex II attached to this Directive;

3) Where a private limited company has 10 or more shareholders or its total assets exceed Birr 10,000,000 (ten million), it shall submit an audit report prepared by an independent and impartial external auditor;

4) A limited liability business organization shall not be required to submit an audit report for renewal;

5) The audit report to be submitted by a limited liability business organization for renewal shall not exceed /be older than/ two fiscal years;

6) Where the capital of private limited companies is reduced by 3/4th, the board of directors, if any, or the general manager of the company shall cause the issue, whether to dissolve the company or not, to be determined by shareholders. Where shareholders of the company resolved in favor of the continuation of the company, it shall cause the license to be renewed by raising the capital of the company to more than 1/4th.

7) Provided however, where the increase of

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ሳይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 30 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
3. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር 10 እና ከዚያ በላይ ባለ አክስዮኖች ያሉት እንደሆነ ወይም የማኅበሩ ጠቅላላ ሃብት ከብር 10,000,000 /ዐሥር ሚሊዮን ብር/ በላይ ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት ሲጠይቅ ነጻና ገለልተኛ በሆነ የውጭ ኦዲተር የተሠራ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
4. ኃላፊነቱ ያልተወሰነ የንግድ ማኅበር በዕድሣት ወቅት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም።
5. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር በእድሳት ወቅት የሚያቀርበው የኦዲት ሪፖርት ሁለት የበጀት ዓመት ያሳለፈው መሆን አለበት።
6. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ

the capital has not been implemented within 90 consecutive days as of the reduction of the capital by $3/4^{th}$ is known, any interested party may cause the cancellation of the registration of the company by submitting a court order to dissolve the company to the registering body. The company shall not, under such circumstance, request commercial registration and licensing services other than cancellation;

8) Where three quarters (¾$^{th}$) of the capital of a share company is lost, the board of directors shall call an extraordinary meeting to decide on the dissolution or continuation of the company. Where the shareholders resolve in favor of continuation of the company, they shall cause the license to be renewed by raising the capital to more than one quarter (1/4);
9) Amendments made in the certificate of business registration certificates concerning an increase or a reduction of capital made by traders shall also be recorded in their business licenses;
10) A newly established limited liability business organization shall not be required to submit an audit report for period not exceeding two fiscal years;
11) A business license of a limited liability

| | |
|---|---|
| በ¾ኛ ከጎደለ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ሥራ አስኪያጆች ስለ ማኅበሩ መፍረስ አለመፍረስ በባለአክሲዮኖች እንዲወሰን በማድረግ ባለአክስዮኖች ማኅበሩ እንዲቀጥል በቃለ ጉባኤ የወሰኑ እንደሆነ ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ የማኅበሩን ፈቃድ ማሳደስ ይችላሉ። | business organization may be renewed upon application by the general manager of the company or a person legally delegated to perform such act on behalf of the company; |
| | 12) A tax clearance certificate submitted in a place where information network is available shall be verified by a body authorized by law through such network; |
| 7. ሆኖም ዋና ገንዘቡ በ¾ኛ መጉደሉ ከታወቀ አንስቶ በ90 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካልተፈጸመ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ የፍርድ ቤት የማፍረሻ ትዕዛዝ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብ የንግድ ማኅበሩ እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል። በዚህን ጊዜ ማኅበሩ ከሥረዛ በስተቀር ማንኛውንም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቅ አይችልም። | 13) A ax clearance certificate submitted in place where information network is not connected with tax office, the submitted tax clearance certificate shall be deemed to have been issued by a body authorized by law to collect tax;<br>14) Without prejudice to the provisions of Sub-articles 12 and 13 of this Article, the registering body shall verify the authenticity of the submitted tax clearance /certificate/ by all available means; |
| 8. የአክስዮን ማኅበር የዋና ገንዘቡን ¾ኛ በኪሣራ ያጣ እንደሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ የማኅበሩን መፍረስ ወይም መቀጠል የሚወስን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አለበት። ባለአክስዮኖችም ማኅበሩ እንዲቀጥል በቃለ ጉባኤ የወሰኑ እንደሆነ ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ | 15) A trader, who was previously engaged in any business by obtaining a business license under any category and whose license has been cancelled for any reason, or who is under penalty, shall submit a tax clearance certificate concerning the previous business license in order to obtain a new business license; |

| | |
|---|---|
| የማኅበሩን ፈቃድ ማሳደስ ይችላሉ። | |
| 9. የካፒታል ጭመራ ወይም ቅነሳ ያደረጉ ነጋዴዎች በንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀታቸው ላይ የተደረገው ማሻሻያ/ለውጥ/ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውም ላይ ይመዘገባል። | 16) The relevant directive shall be applicable to categories of Business licenses required to have certificate of competence. |
| 10. አዲስ የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር እስከ ሁለት የበጀት አመት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም። | **20. Amendment of Business License** |
| 11. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር የንግድ ሥራ ፈቃድ ስማሳደስ የንግድ ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማኅበሩን ወክሎ በማኅበሩ ስም ይህንን ጉዳይ እንዲያስፈጽም ሕጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው መታደስ ይችላል። | 1) Where a trader requests a service for amendment business license, a request for amendment of business license shall be submitted by filling out Form 03 of Annex I attached to this Directive; |
| 12. የመረጃ መረብ ባለበት ቦታ ሁሉ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ ግብር ለመሰብሰብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የመረጃ መረብ መረጋገጥ አለበት። | 2) Where it is ascertained that the requirements are met as provided for in Article 32 of the Regulation, the amendment shall be posted on the system where online service is provided or where online service is not available, the trader shall be issued with the amended business license as prescribed in Form 02 of Annex II attached to this Directive by returning the previous original business license; |
| 13. ግብርን ለመሰብሰብ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር የመረጃ መረብ ግንኙነት በሌለበት ቦታ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ግብር ለመሰብሰብ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠው መረጃ ትክክለኛ ነው | 3) Where the vehicles belong to traders engaged in /transport/service business, their business licenses shall be amended if the number vehicle has increased or the type of vehicle has changed by having the chassis and plate numbers registered, or |

| | |
|---|---|
| ተብሎ ይወሰዳል። <br>14. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 እና 13 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ መዝጋቢው አካል የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ ማረጋገጥ አለበት። <br>15. ቀደም ሲል በየትኛውም የሥራ መደብ የንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ ቆይቶ በማንኛውም ምክንያት የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም በቅጣት ላይ ያለ ነጋዴ አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲያወጣ ቀድሞ ሲሰራበት ስነበረው የንግድ ሥራ ፈቃድ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት። <br>16. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ሥራ ፈቃድ መደቦችን በተመለከተ አግባብነት ባለው መመሪያ በተወሰነው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል። <br><br>**20. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለ ማሻሻል** <br>1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ የማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል <br>2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ | if it is a different service sector, by having the amendment or change registered. <br><br>**21. Substitute Business License** <br>1) Where a trader requests a service for substitute of business license, a request for amendment of business license shall be submitted by filling out Form 03 of Annex I attached to this Directive; <br>2) substitute business license shall be issued as prescribed in Form 02 of Annex II attached to this Directive if it is ascertained that requirements provided for in Article 33 of the Regulation are met; <br>3) Without prejudice to Sub-article (1) of this Article, when the service is provided online, the customer may directly obtain a substitute business license from the online system. <br>**22. Cancellation of Business License** <br>1) Where a trader requests a service for cancellation of business license, a request for amendment of business license shall be submitted by filling out Form 03 of Annex I attached to this Directive; <br>2) Where it is ascertained that the requirements are met as provided for in Article 35 of the Regulation, the amendment shall be posted on the |

አንቀጽ 32 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ማሻሻያው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ሥራ ፈቃድ ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት የተሻሻለ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. የአገልግሎት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ተሽከርካሪ ከሆነ ብዛቱ ከጨመረ ወይም ተሽከርካሪው በተለወጠ ጊዜ የቻንሲ እና የሰሌዳ ቁጥር በማስመዝገብ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዘርፍ ከሆነ የተደረገውን ማሻሻያ ወይም ለውጥ በማስመዝገብ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸው እንዲሻሻል ይደረጋል።

**21. ስለ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ**

1. ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ

system where online service is provided or where online service is not available, the trader shall be issued with the letter of cancellation by returning the previous original business license;

3) Every cancellation of business license shall be notified by a letter to the person who has requested the cancellation and the concerned organ;
4) Where three quarters (3/4) of the capital of limited liability business organizations is lost and the board of directors, if any, or the manager is unable to raise the capital to more than 1/4, any interested party may cause the company to be cancelled by submitting the order of dissolution of a court to the registering body. The organizations shall not, under such circumstance, request any other commercial registration and business licensing services other than cancellation;
5) Where there quarters ( ¾ ) of the capital of a share company is lost due to bankruptcy, the board of directors shall call an extraordinary meeting to decide on the dissolution or continuation of the company. Where the shareholders are unable to resolve in favor of raising the capital to be more than one quarter (1/4), any interested party may cause the cancellation of the registration of the

አንቀጽ 33 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሠረት ምትክ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶች በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጡበት ጊዜ ተገልጋዩ በቀጥታ ምትክ ማውጣት ይችላል።

**22. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ**

1. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅጽ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ላይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል።
2. የተጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 35 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎቱ በበይነ መረብ /ኦንላይን/ በሚሰጥባቸው ቦታዎች የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛው ሲስተሙ ላይ እንዲታይ በማድረግ እንዲሁም ኦንላይን አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነበት ቦታ ነጋዴው ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እንዲመልስ በማድረግ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ ማስረጃ ደብዳቤ

company by submitting a court order to dissolve the company to the registering body.

## PART FIVE

## SPECIAL REGISTRATION, RENEWAL, AMENDMENT, SUBSTITUTE AND CANCELLATION

**23. Registration of Sectoral Association and Branch Offices of Foreign Chambers of Commerce and Special Registration of Holding Company or Franchising**

1) Where an applicant requests a service for registration of sectoral association and branch Offices of foreign chambers of commerce and special registration of holding company or franchising, a request shall be submitted by filling out the application Form 04 of Annex 1 attached to this directive;
2) Where the requested service:
   a) fulfills the requirements provided for in article 16 of the Regulation, a certificate registration of sectoral association shall be issued as prescribed in Form 06 of Annex II attached to this Directive;
   b) fulfills the requirements provided for in the Regulation, a certificate of registration of branch office of foreign chamber of commerce shall be issued as prescribed in Form 07 of Annex II

ይሰጣል።

3. ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

4. ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራት የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በ¾ኛ ከጎደለ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ካለ ቦርዱ ወይም ሥራ አስኪያጆች ዋና ገንዘቡን ከ1/4ኛ በላይ እንዲሆን ማድረግ ካልቻሉ ጥቅም ያለው ሰው ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የማፍረሻ ትዕዛዝ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብ የንግድ ማኅበሩ እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል። በዚህን ጊዜ ማኅበሩ ከሥረዛ በስተቀር ማንኛውንም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቅ አይችልም።

2) The inspector shall cause administrative measures to be taken in accordance with Sub-article (2) of Article 29 and Sub-article (2) of Article 28 of the Proclamation against those traders who is engaged in business without renewing his business license based on the findings of the inspection.

**55. Inspection and verification of fulfillment of requirements for commercial registration and business license**

1) The inspector shall, by inspecting and verifying the fulfillment of the requirements through internal inspection, submit a recommendation to his immediate boss by organizing information on any trader who has obtained a business license without fulfilling the requirements applicable for commercial registration and business licensing in accordance with the Proclamation and Regulation or by submitting false information.

2) The inspector shall, based on the findings of the inspection, cause administrative measures to be taken in accordance with Sub-article (1)(d) and Sub-article (3) of Article 49 of the Proclamation against a trader who has

ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን የማጣራትና የማረጋገጥ፤

2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሯቸው ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጭ የሚሰሩትን የንግድ ድርጅቶች የማጣራትና የማረጋገጥ፤
3. በንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት ጊዜ ውስጥ የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የሚሰሩ የንግድ ድርጅቶችን የማጣራትና የማረጋገጥ፣
4. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች አሟልቶ አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ከንግድ ድርጅቶች ፋይል ወይም ሰነድ የማጣራት እና የማረጋገጥ፤
5. ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 26 መሠረት የተጣለበትን ግዴታዎች አሟልቶ መሥራቱን የማጣራትና የማረጋገጥ፣
6. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሕጎች መሠረት ያገኘውን መብት ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠትን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
7. የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነት የማጣራትና የማረጋገጥ።

obtained a business license without fulfilling the requirements or by submitting false information.

## 56. Ensuring fulfillment of obligations

1) In order to ensure that the trader has fulfilled his obligations in accordance with Article 26 of the Proclamation, the following shall be inspected and verified by external inspection:

   a) availability of the trader at the address he has registered;
   b) whether the merchant has registered a change of address;
   c) wholesale to wholesale or retail to retail transactions are being carried out at the same level;
   d) whether the trader has provided correct information when requesting business registration and licensing services;
   e) ensure that the price list of goods or services is displayed in a clearly visible place or price tags are affixed on the goods;
   f) ensure that business activities of various goods that endanger public health and safety or property are carried out in the same places or premises.

**52. የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ስለማጣራት**

1. በአዋጁ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በንግድ መደብር ውስጥ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ነጋዴ እየሰራ ባለው የሥራ ዘርፍ በዘመኑ የተሰጠ ወይም የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ)፣ (ሐ) እና አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ)፣(ሐ) መሠረት በታገደ ወይም በተሰረዘ የንግድ ሥራ ፈቃድ እየተሠራ አለመሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም በታገደ እና በተሰረዘ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰሩትን ለኢንስፔክሽን ሥራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላትና ተጨማሪ መረጃ በመያዝ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል።
4. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም በተሰረዘ የንግድ

2) The inspector shall submit recommendation to cause administrative measures to be taken by incorporating information as per the checklist stated in Form 01 of Annex IV attached to this Directive by identifying those traders who have not fulfilled the obligations imposed on them as provided in Sub-articles (1) to (6) of this Article.

3) A trader who has not fulfilled the obligations imposed on him in accordance with Sub-article (2) of this Article shall be issued with written notice to remedy his deficiency.

4) Where the trader fails to remedy its deficiency, additional administrative and legal measures shall be taken by organizing the information related thereto.

**57. Inspecting and verifying business license transferred to third party**

1) The inspector shall submit a recommendation to his immediate boss by incorporating the information as per the checklist stated in Form 01 of Annex IV attached to this Directive which is prepared for inspection purpose where it is proved that the trader has surrendered

ሥራ ፈቃድ በሚሰሩ ነጋዴዎች ሳይ በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

**53. ከተሰጣቸው የንግድ ሥራ ፈቃድ የሥራ መደብ ውጭ የሚሰሩትን ስለማጣራት**

1. ማንኛውም ነጋዴ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ነገር ግን እየሠራ ያለው ከተፈቀደለት የንግድ ሥራ መደብ ውጭ መሆኑን በኢንስፔክሽን ሥራ በማጣራትና በማረጋገጥ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ኃላፊ ያቀርባል።
2. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ከተፈቀደለት የንግድ ሥራ መደብ ውጭ በሚሰራ ነጋዴ ሳይ በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አግባብ ባለው ባለሥልጣን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

**54. የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያሳድሱ የሚሠሩ ነጋዴዎችን ስለማጣራት**

1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በበጀት ዓመቱ ባልታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ እየሰራ መሆኑን በማጣራትና

or leased his license to third party to allow the latter to conduct business or has surrendered or leased the same to foreigners who are not allowed to do business.

2) The inspector shall cause administrative measures to be taken by the appropriate authority and bring the trader before a court of law by organizing the necessary information where the trader has surrendered his license to third party in accordance with Sub-article (1) (b) of Article 29 and Sub-article (4) of Article 49 of the Proclamation.

**58. Inspecting and verifying Enforcement of administrative measures**

The relevant authority shall take administrative measures against business organizations who do not implement the measures taken against them and bring them before a court of law after having inspected and verified the implementation of the administrative and legal measures taken for violation of the provisions of the Proclamation, Regulations and this Directive by external inspection.

**59. Duties and obligations of external post-licensing Inspector**

External post-licensing Inspector shall have the following duties and obligations:

| | |
|---|---|
| በማረጋገጥ ለኢንስፔክሽን ሥራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ኢንስፔክተሩ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል<br>2. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያሳድስ የሚሰራ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ29 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።<br>**55. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት የተቀመጠው መስፈርት ተሟልቶ አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ከነጋዴው ፋይል ወይም ሰነድ ስለማጣራት እና ስለማረጋገጥ**<br>1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ እና በደንቡ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማግኘት የተቀመጡ መስፈርቶች ተሟልተው አገልግሎት ስለመሰጠቱ በውስጥ ኢንስፔክሽን ሥራ በማጣራትና በማረጋገጥ መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ባገኘ ነጋዴ ላይ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ኢንስፔክተሩ መረጃ በማደራጀት የውሳኔ ሃሳብ ለቅርብ | 1) show his special identification card that indicates his status to the inspected business organization;<br>2) explain to the inspected business organization about the purpose of inspection;<br>3) notify immediately to the owner of the business organization or his representative about the defect observed the process of inspection;<br>4) reach an agreement with the appropriate officer assigned to coordinate the inspection activities concerning the business organization to be inspected as prescribed in Form 02 attached as Annex IV to this Directive before he goes out for inspection activities;<br>5) perform his inspection duties only during government working hours, provided however, when it is necessary to carry out inspection outside of government working hours and show a special letter issued by the office addressing the business organization;<br>6) fill out the findings of the inspection in Form 01 of Annex IV attached to this Directive and sign on the same jointly with the inspected business organization; if the trader is not willing to sign, notify such refusal to his |

ኃላፊው ያቀርባል።

2. በውስጥ ኢንስፔክሽን ውጤት መሠረት መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ያገኘ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1/መ እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

**56. ነጋዴው በአዋጁ አንቀጽ 26 መሠረት ግዴታዎችን ስለማሟላቱ የሚደረግ ማጣራት**

1. ነጋዴው በአዋጁ አንቀጽ 26 መሠረት ግዴታዎችን ስለማሟላቱ ለማጣራትና ለማረጋገጥ የሚከተሉት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡-
   - ሀ) ነጋዴው ባስመዘገበው አድራሻ የሚገኝ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤
   - ለ) ነጋዴው የአድራሻ ለውጥ አድርጎ ያስመዘገበ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤
   - ሐ) ጅምላ ከጅምላ ወይም ችርቻሮ ከችርቻሮ በተመሳሳይ ደረጃየሚደረግ ግብይት እየተፈፀመ ያስመሆኑን የማጣራትና የማረጋገጥ፤
   - መ) ነጋዴው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ ትክክለኛ መረጃዎችን በማቅረብ ያስመዘገበ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤

immediate boss with his recommendation;

7) carry out administrative measures based on the inspection findings and the decision of the relevant authority;

8) ensure that the business organization has taken remedial measure to correct the defect observed by appearing in person at premises of the business organization;

9) take administrative measure in the presence the trader or a person delegated to carry out the business and, where necessary, a security officer If he carries out affixing of seals on the business organization.

**60. Rights and obligations of inspected traders**

1) The inspected trader shall have the following rights:
   - a) request and see the special identification card of the inspector that reveals his identity;
   - b) request and acquire any information concerning the inspection work;

2) The inspected trader shall have the following obligations:
   - a. open his business premises during working hours and, when necessary, outside working hours

ሠ) የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዋጋ ዝርዝር በግልጽ በሚታይ ቦታ መቀመጡን ወይም በንግድ ዕቃዎች ላይ መለጠፉን የማጣራትና የማረጋገጥ፤

ረ) በተጠቃሚው ሕዝብ ጤንነትና ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተለያዩየንግድ ዕቃዎች በአንድ ስፍራእያካሄደ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን ሥራየማጣራትና የማረጋገጥ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ነጋዴ በመለየት ለኢንስፔክሽን ሥራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ኃላፊው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ግዴታውን አልተወጣም ተብሎ የተለየ ነጋዴ ጉድለቱን እንዲያስተካክል አግባብ ባለው ኃላፊ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይሰጠዋል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ነጋዴው ጉድለቱን ያላስተካከለ ከሆነ መረጃ ተደራጅቶ ተጨማሪ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

**57. በአዋጁ መሠረት ነጋዴው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠቱን ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ**

for purposes of inspection;

b. make available his business license and other business related information that he is obliged to provide.

**61. Procedure for taking administrative measures**

1) The Inspector shall submit his recommendation by compiling the information and reports on defects found during the inspection.

2) The immediate authority shall render decision on the findings and recommendation of the Inspection based on the Proclamation and Regulation or shall cause to be rendered by higher authority.

## PART TEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**62. Duty to cooperate**

Any person shall have the obligation to cooperate in the implementation of this directive based on article 48 of the proclamation.

**63. Inapplicable Directives**

Any other directive or practice inconsistent with the provisions of this Directive shall not

1. በውጭ ኢንስፔክሽን ውጤት እና በሚቀርብጥቆማ መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃዱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲነግድበት የሰጠ ወይም ያከራየ እንዲሁም በሕግ እንዲነግዱ ሳልተፈቀደላቸው የውጭ አገር ዜጎች የንግድ ሥራ ፈቃዱን አሳልፎ የሰጠ ወይም ያከራየ ነጋዴ በማጣራት እና በማረጋገጥ ኢንስፔክተሩ ለኢንስፔክሽን ሥራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅጽ 01 ቼክሊስት መሠረት መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃዱን አሳልፎ ለሦስተኛ ወገን ሰጥቶ በተገኘ ነጋዴ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1(ሰ) እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት አግባብ ባለው ኃላፊ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ እና አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጀት ለሕግ እንዲቀርብ ይደረጋል።

**58. የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነት ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ**

የአዋጁ፣ የደንቡ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመጣሳቸው የሚወሰደውን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ በትክክል ተግባራዊ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን የማጣራት እና የማረጋገጥ ሥራ በማከናወን

be applicable.

**64. Repealed Directives**

Business Registration, Licensing and Post-licensing Inspection previously called Directive No. 010/2017 and registered as Directive No. 528/2021 by the Ministry of Justice in accordance with Proclamation No. 1183/2000 is hereby repealed.

**65. Effective Date**

This directive shall be effective from the date it is Registered and aploaded on the Ministry of Justice website.

Gebremeskel Chala

Minister of the Ministry of Trade and Regional Integration of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

ተግባራዊ ባላደረጉት ነጋዴዎች ላይ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ መረጃዎችን በማደራጀት ለሕግ እንዲቀርቡ ይደረጋል።

**59. የውጭ ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክተር ሊፈጽማቸው የሚገባው ተግባራት እና ግዴታዎች**

ማንኛውም ኢንስፔክተር የሚከተሉት ተግባራትና ግዴታዎች አሉበት፡-

1. ኢንስፔክተር መሆኑን የሚገልፅ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ኢንስፔክሽን ለሚካሄድበት የንግድ ድርጅት የማሳየት፤
2. ኢንስፔክሽን ለሚካሄድበት የንግድ ድርጅት ስለሚደረገው ኢንስፔክሽን የማስረዳት ፤
3. በኢንስፔክሽን ሥራ የታየውን ጉድለት ለንግድ ድርጅቱባለቤት ወይም ተወካይ ወዲያውኑ የማሳወቅ፣
4. ለኢንስፔክሽን ሲወጣ ሥራውን ለማስተባበር ከተመደበው አግባብ ያለው ኃላፊ ጋር ኢንስፔክሽን ስለሚካሄድበት የንግድ ድርጅት እና ስለሚደረገው ኢንስፔክሽን ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ IV በሆነው ቅጽ 02 መሠረት ስምምነት የማድረግ ፤
5. የኢንስፔክሽን ተግባሩን የሚያከናውነው በመንግሥት የሥራ ሰዓት ብቻ ሆኖ ነገር ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት የሥራ ሰዓት

| | |
|---|---|
| ውጪ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ የንግድ ድርጅቱን ስም የሚገልፅ ልዩ ደብዳቤ ከመሥሪያ ቤቱ የመያዝና የማሳየት፤<br>6. ባደረገው የኢንስፔክሽን ተግባር ያገኘውን ውጤት በዚህ መመሪያ አባሪ IV ቅጽ 01 በመሙላት እና ኢንስፔክሽን ከተካሄደበት የንግድ ድርጅት ጋር በመፈራረም፣ ነጋዴው ለመፈራረም ፈቃደኛ ካልሆነም ይህንኑ ገልጾ ለቅርብ ኃላፊው ከውሳኔ ሀሳብ ጋር የማቅረብ፣<br>7. በቀረበው የኢንስፔክሽን ውጤት እናአግባብ ያለው ኃላፊ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የተወሰነውን አስተዳደራዊ እርምጃ የመፈጸም፤<br>8. አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት የንግድ ድርጅት የታየበትን ጉድለት ስለማስተካከሉ በድጋሚ በንግድ ድርጅቱ በመገኘት የማረጋገጥ፤<br>9. የንግድ ድርጅት እሸጋ የሚያከናውን ከሆነ ነጋዴው ወይም ንግዱን ለማከናወን የተወከለ ሰው እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጸጥታ አካል ባለበት አስተዳደራዊ እርምጃውን የመፈጸም።<br>**60. ኢንስፔክሽን የሚደረግበት ነጋዴ መብትና ግዴታ**<br>1. ኢንስፔክሽን የሚካሄድበት ማንኛውም ነጋዴ የሚከተሉት | |

መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኢንስፔክተሩን ማንነት የሚገልፅ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት የመጠየቅና የማየት፤

ለ) የኢንስፔክሽን ሥራውን በተመለከተ ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የማግኘት።

2. ኢንስፔክሽን የሚካሄድበት ማንኛውም ነጋዴ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) ለኢንስፔክሽን ሥራ የንግድ ሥራ ቦታውን በሥራ ሰዓት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ ስዓት ውጭ ክፍት የማድረግ፤

ለ) የንግድ ሥራ ፈቃድ እና ሌሎች ከንግድ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግዴታ የገባባቸውን መረጃዎች ይዞ የመገኘት።

**61. የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ሥርዓት**

1. ኢንስፔክተሩ በኢንስፔክሽን የተገኙ ጉድለቶችን በመረጃና በሪፖርት በማጠናቀር ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል።
2. የቅርብ ኃላፊው በቀረበው የኢንስፔክሽን ውጤት እና የውሳኔ ሀሳብ ላይ በመመስረት እና በመረጃ በማስደገፍ ከአዋጁና ደንቡ ጋር አገናዝቦ ውሳኔ ይሰጣል ወይም እንደአግባቡ በበላይ ኃላፊ ውሳኔ

እንዲሰጥ ያደርጋል።

## ክፍል አሥር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**62. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት በአዋጁ አንቀጽ 48 መሠረት የመተባበር ግዴታ አለበት።

**63. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች**

በዚህ መመሪያ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሠራር ወይም ልማድ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**64. የተሻሩ መመሪያዎች**

መመሪያ ቁጥር 10/2009 ተብሎ የሚታወቀውና በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት በፍትሕ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 528/2013 ሆኖ የተመዘገበው የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

**65. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ገብረመስቀል ጫላ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

| | |
|---|---|
| | |

# አባሪዎች
# Annexes

## አባሪ I
## Annex I

# የንግድምዝገባናፈቃድአገልግሎትመጠየቂያየማመልከቻቅጾች
# COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING SERVICE REQUEST APPLICATION FORM

ኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
የንግድናቀጣናዊትስስርሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade and Regional Integration

አባሪ፣ ቅጽ 01

—— ቀን —— ወር ——— ዓ.ም.

**የአገልግሎትመጠየቂያቅጽ**
**Service Request Form**

**1/ የጠየቁትአገልግሎትዓይነት[—√"ምልክትበማድረግይግለፁ]**
Type of Service requested

☐ የድርጅትስም/የንግድስምማጣሪያ
Busiess/trade name

☐ አዲስንግድምዝገባ
New commercial registration

☐ አዲስ ንግድ ስራ ፈቃድ
New business license

☐ ሻያ /ምዝገባ/ ንግድፈቃድ
Amendment/registration/business license

☐ ድርጅትስም/ንግድስም
Business name/trade name

☐ የንግድፈቃድዕድሳት
Renewal of business license

☐ ስረዛ /ምዝገባ/ ንግድፈቃድ፣
Cancellation/registration/business license

☐ ድርጅትስም/ንግድስም
Business name/trade name

☐ ምትክ /ምዝገባ/ ንግድፈቃድ፣
Substitute/registration/business license

☐ ድርጅትስም/ንግድስም
Business name/trade name

ሌላ ከሆነ ይግለፁ ______________________________
Provide here if it is different

**2/አመልካች**
**Applicant**

**2.1/ግለሰብነጋዴ**
**Sole proprietor**

ሀ. ሙሉስም ______________________
A. Full name ______________________
ለ. የእናትስም ______________________
B. Mother's name
ሐ. ጾታ ሴ ☐ ወ ☐
C. Gender Female Male

መ. ዕድሜ ______________________
D. Age ______________________
ሠ. ዜግነት ______________________
E. Nationality ______________________
ረ. የግብርከፋይመለያቁጥር ______________________
F. Tax Identification Number ______________________

**2.2/የንግድማህበር**
ሀ. የማህበሩ የንግድ ስም ______________________

A. Trade name ___________________________

ለ. የስራ አስኪያጅ ሙሉ ስም ___________________

B. Full name of the Manager

ሐ. ሕጋዊአቋም

C. Legal status

የኅብረትሽርክና ማኅበር ሁለትዓይነትኃላፊነትያለበትየሽርክናማኅበር ☐

General partnership/Limited partnership

ኃላፊነቱየተወሰነየሽርክናማኅበርአክስዮንማኅበር ☐

Private Limited Company and Share Company

ኃላ/የተ/የግ/ማ ባለአንድአባል ኃላ/የተ/የግ/ማ

Private Limite Company ☐ One Memaber Private Limited Company ☐

2.3/ በውጭአገርየተቋቋመየግለሰብማህበር

**Business organization incorporated abroad**

ሀ. የተቋቋመበትአገር ___________________

Country of incorporation

ለ. የንግድስራውዓይነት/ዋናዘርፍ ________________

Type of business/Main sector

3/የንግድሥራአድራሻ

**Business address**

ሀ. ክልል ____________ ከተማ/ዞን ____________ ወረዳ/ቀበሌ ____________

A. Region City/Zone Woreda/Kebele

ለ. ከተማ ____________ ክፍለከተማ____________ ወረዳ/የቤ/ቁ ____________

B. City ____________ Sub-city ____________ Woreda/H.No ____________

ሐ. የቢሮስልክ ____________ ሞባይል ____________

C. Office tel. No. Mobile ____________

መ. ፋክስ ____________ ኢ-ሜይል ____________

D. Fax ____________ E-mail ____________

ሠ. ፓ.ሣ.ቁ ____________

4/ ለንግድስራውየተመዘገበውካፒታል

**Business Registered capial**

ሀ. የተፈረመ/የፀደቀ ብር ________________

A. Subscribed/approved capital

ለ. የተከፈለብር ____________________

B. Paid up capital

ሐ. ጠቅላላየአክሲዮንብዛት____________________

C. Total Number of shares

መ. የአንድ አክስዮን ዋጋ ብር____________________

D. Per value of share

5 /የጠየቁትየአገልግሎትዓይነት

**Service requested**

5.1/አዲስየንግድምዝገባ/ማሻሻያ/የአድራሻለውጥ /ምትክ/ ስረዛ /የጠፋ/ የተበላሸከሆነ፣

**New commercial registration/Amendment/ change of address/substitute/cancellation/lost/damaged**

ሀ. በባለፈቃዱ/ በግለሰቡ/የንግድማህበሩስምላይለውጥካለበተ/ቁጥር (2.1) ወይም

A. (2.2) ወይም (2.3) የተዘጋጀባዶቦታላይይሙሉ

A. Enter the information in the space provided in No. (2.1) or (2.2) or (2.3) if there is a change in the business name of the Licensee/individual

ለ. የተለወጠአድራሻ (ካለ)

B. Cahnge of address, if any

ክልል ____________ ከተማ/ዞን ____________ ወረዳ/ቀበሌ ____________

Region ____________ City/Zone ____________ Woreda/Kebele ____________

ከተማ ______________ ክፍለከተማ _____________ ወረዳየቤ/ቁ ____________
City _______________ Sub-city _____________ Woreda/H.No _____________
የቢሮስልክ _______________ ሞባይል ____________________
Office tel. no. _________________ Mobile__________________
ሌሳ ከሆነ ይግለፁ ________________________________________
Provide here if it is different ______________________________

ሐ. የተሰረዘው/የተሰረዙትየንግድስራፈቃድቁጥር/ቁጥሮች _________________________
C Number/s of the cancelled license or licenses _________________________
መ. የሚመለሰውምዝገባቁጥር _____________________________________
Registration number to be returned _____________________________

**5.2 የንግድስምማጣሪያየምስክርወረቀትማግኘትከሆነ**

Obtaining of certificate for verification of trade names

ሀ. የባለፍቃዱን /የግለሰቡ/ የንግድማህበሩንሙሉስምማጣራትቢያስፈልግዎስሙንበተ/ቁ (2.1) ወይም(2.2) ወይም (2.3) ከተገለፀውባዶቦታላይይሙሉ

A. Enter the information in the space provided in No. (2.1) or (2.2) or (2.3) if it is a request for verification of the full name of the licensee/individual/business organizations

ለ. በተ/ቁ (3) ስር በተገለፀው ባዶ ቦታ ላይ አድራሻውንይሙሉ

B. Enter the address in the space provided in No. (3)

ሐ. እንዲጣራየጠየቁትንየድርጅት/የንግድስምበቅድምተከተልስሙንበአማርኛናእንግሊዘኛይፃፉ

C. Provide the business/trade name for which a request for verification is made in Amharic and English, respectively

4) በአማርኛ – ______________________________________________
In Amharic ________________________________________
በእንግሊዝኛ – ____________________________________________
In English ____________________________________________

2. በአማርኛ – ______________________________________________
In Amharic ________________________________________
በእንግሊዝኛ– ______________________________________________
In English ____________________________________________

3. በአማርኛ– ______________________________________________
In Amharic ________________________________________
በእንግሊዝኛ– ______________________________________________
In English ____________________________________________

**6/ማረጋገጫ**

**verification**

11115፣11311፣35411፣36811፣36911፣39141፣51114፣51213፣61511፣61711፣62314፣62714፣63119፣64111፣65412፣65221፣65615፣65753፣65811፣66131፣66212፣66217፣66331፣72131፣84112፣84116፣85121፣85211፣85212፣86116፣86316፣86318፣86411፣86511፣86513፣91113፣91411፣92127፣92131፣93111፣93123፣93211፡-

በዚህየንግድሥራፈቃድመስጫመደብያለብቃትአረጋጋጭመስሪቤትምስክርወረቀትመስራትየማይቻልመሆኑን። ተገንዝቤፈቃዱንካወጣሁበኋላብቃትአረጋጋጭመ/ቤትበመሔድየብቃትማረጋገጫሰርተፊኬትየምወስድመሆኔንእናበዚህማመልከቻቅጽውስጥየተገለጹትየተሞሉትናበአባሪነትአያይዤያቀረብኳቸውማስረጃዎችበሙሉትክክልመሆናቸውንበፊርማዬአረጋግጣለሁ።

I fully understand that it is not allowed to operate a business falling under this category without having the respective competency certificate issued by the concerned office and hence shall obtain the certificate from the office and solemnly affirm by my signature that the information or statement provided in this form and the attached documents is correct.

የአመልካቹሙሉስም ______________________

Full name of the applicant ______________________

ፊርማ ____________________________________________

Signature ________________________________________

ቀን ______________________________________

Date ______________________________________

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

**<u>N.B</u>**

ሀ. ይህንቅጽከሞሉበኋላማቅረብስለሚጠበቅብዎትማስረጃየአባሪውንዝርዝርይመልከቱ፤

A. Refer the Annex with respect to documents required to be submitted

ለ. የንግድደርጅት በ6 ወርጊዜውስጥበን/ኢ/ሚ ማዕከላዊየመረጃቋትላይካልተመዘገበእንደተመዘገበአይቆጠርም፤

B. business organization, which is not registered or entered in the central data base of the Ministry of Industry within 6 months, shall be deemed not to have been registered

ሐ. የተሻሻለውየንግድስም/ድርጅትስምእስከሁለትወራትጊዜውስጥፀድቆለሚመዘገበውአካልቀርቦካልተመዘገበ እንደተሻሻለአይቆጠርም።

C. A trade name or business name shall not be deemed to have been amended if the amended name is approved and registered with the relevant body within two months

**1.አባሪ**

**Annex**

ሀ. የግብርከፋይመለያቁጥርሰርተፊኬትኮፒ

A. Photocopy of Tax Identification Number (TIN)

ለ. የአመልካችየታደሰየቀበሌመታወቂያ /የሚሰራፓስፖርት/የመንጃፈቃድ/የመሥሪያቤትመታወቂያ/ፎቶኮፒ.........

B. Photocopy of valid Identification card/passport/driving license/employee ID

ሐ. አመልካቹ 6 ወርባልሞላጊዜውስጥየተነሳው 4 ፓስፖርትመጠንያለውጉርድፎቶግራፍ

C. Four passport size photographs taken within the preceding six months

መ. ምትክጥያቄከሆነየንግድምዝገባ፣ የንግድፈቃድየተበላሸከሆነየተበላሸውንመመለስ

D. Return the business license if the request is for substitute or the damaged business license if the business license is damaged

ሠ. የጠፋከሆነከሚመለከተውአካልማስረጃማቅረብ

E. Submit evidence given from concerned bodyif the business license is lost

ረ. የተጠየቀውየንግድስራመስክየብቃትማረጋገጫየሚያስፈልገውከሆነማቅረብ

F. Submit certificate of competence if required

ሰ. ስንግድፈቃድዕድሳትየግብርክሊራንስማቅረብ

G. Submit tax clearance for renewal of license

ሸ. ማሻሻያከሆነየተሰጠውንየንግድምዝገባዋናሠርተፊኬት፣የንግድፈቃድዋናሠርተፊኬት

H. Submit the original certificate of commercial registration and business license if it is a request for amendment

አመልካቹየንግድማህበርከሆነከላይከተገለጸውበተጨማሪ

If the applicant is a business organization, it shall, in addition to the above, submit:

ሀ. የፀደቀመመሥረቻጹሁፍእናመተዳደሪያደንብፎቶኮፒ፣

A. Photocopies of the authenticated memorandum of association *and Articles of Association*?

ለ. አክሲዮንማህበርከሆነተፈርሞየፀደቀካፒታልአንድአራተኛ (1/4) በባንክዝግሂሳብተቀማጭመደረጉንየሚገልጽማስረጃ ፣

B. Submit evidence showing that 1/4th of the subscribed and approved capital has been deposited in a blocked account , if it is a shre company

ሐ.የመንግሥትልማትድርጅትወይምማናቸውምየንግድዓላማያለውበጎአድራጎትድርጅትወይምሌላተቋምከሆነየተቋቋመበትንአዋጅወይ ምደንብእንዲሁምየሥራአስኪያጁንየሹመትደብዳቤማቅረብ፣

C. Submit the establishment Proclamation or Regulation and letter of appointment of the manager if it is a public enterprise or any other organization or a certificate of registration and letter of appointment of the manager if it is a civil society organization with business objective

መ. የውጭሀገርዜጋ

D. Foreign investor

ማህበርከሆነከሚመለከተውየመንግሥትአካልየተሰጠየኢንቨስትመንትፈቃድእናየግለሰቡየታደሰፓስፖርትእናገፃችፎቶኮፒማቅረብአለበት።

Submit investment permit issued by the concerned government body and photocopies of the relevant pages of the valid passport of the manager

ሠ. ማሻሻያከሆነየተሰጠውንየንግድምዝገባዋናሠርተፊኬት፣የንግድፈቃድዋናሠርተፊኬትእናማሻሻያየሚደረግባቸውን ማስረጃዎች /በህግአካልየፀደቀዋናቅጁቃለጉባኤ/

E. Submit the original Certificate of registration and business license and documernt evidencing the amendments made/original minutes authenticated by the body authorized by law

---

**ለመ/ቤቱአገልግልትብቻ**

**For office use only**

ከላይየቀረበውማመልከቻበንግድምዝገባናፈቃድአዋጅ 980/2008 እናበማሻሻያአዋጅቁጥር 1150/2012

/መሠረትትክክለኛእናመረጃዎችየተሟሉስለሆነብር __________ ከፍለውአገልግልትእንዲያገኙአድርጌያለሁ።

ያረጋገጠውባለሙያሙሉስም ________________

ፊርማ __________

ቀን __________

As the above application is complete in accordance with Proclamation No. 980/2016, I authorize the requested service to be provided with payment of Birr...............

Full name of the approving officer

Signature ______________________

Date _____________________

**አባሪ II**

# የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የምስክር ወረቀቶች

# Annex II

# Bussiness registration and license service certificates

# አባሪ III

# የድርጅት እና የንግድ ስም ማብራሪያ

## የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ ማብራሪያ

የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ የሚከናወነው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 መሠረት ነው። በአዋጁ መሠረት ማንኛውም በንግድ ሥራ ሲሰማራ የሚፈልግ ሰው በንግድ መዝገብ በሚመዘገቡበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ ይኖርበታል።

**የድርጅት እና የንግድ ስም ዓላማ**

የድርጅትና የንግድ ሥም ምዝገባን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ዓላማ በሦስት መልኩ የሚታይ ነው።

- አንደኛው እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ እንዳይሆን ማድረግ ነው።
- ሁለተኛው ደግሞ ሕብረተሰቡ በንግድ ስሙ አማካኝነት ስለንግዱ የተሳሳተ መረጃ እንዳይወስድ ማድረግ ነው።
- ሦስተኛው ዓላማ ደግሞ የንግድ ስሙ ከሞራል ወይም ሥነ- ምግባር ተቃራኒ እንዳይሆን መቆጣጠርነው።

እነዚህ ሦስት ዓላማዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ የንግድ ሥም ድንጋጌዎች ላይ በተለያየ መልኩ ተደንግገው ይገኛሉ። የንግድ ስምን የሚመለከቱት የአዋጁ ዋና ዋና ድንጋጌዎችን ከዚህ በታች ለማብራራት ተሞክሯል።

1.በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገቡት የንግድ ሥሞች ጋር አንድዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች መሆን የለበትም።

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለምዝገባ የቀረበው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋርአንድዓይነት ወይምተመሳሳይና አሳሳች ሲሆን አይገባም።

**ሀ. ቀደምብለው ከተመዘገቡ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ያልሆነ፤**

አንድ ነጋዴ ቀደም ብሎ ከተያዘ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት ስም ማስመዘገብ አይችልም። ምክንያቱም፡-

- ስሙ የንግዱን ዓይነት በግልፅ የማይለይ በመሆኑና ይህም በተለያዩ የንግድ አይነቶች ማንነት ላይ መደናገርን ስለሚፈጥር ፤
- ሕብረተሰቡ ስሙ የትኛውን ንግድ እንደሚያመለክት ለማወቅ ሊቸገር ስለሚችል፤
- ንግዱ በአስፈፃሚ አካላት በቀላሉ የሚለይበት ስም ሊኖረው ስለሚገባ ነው።

የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለመሆኑ ብዙ አስቸጋሪ ሆኖ አይታይም። እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም በንግድ ሥም መዝገቦች ላይ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ብቻ የሚጠይቅ ነው።

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ጉዳዮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል።

- አንደኛው ምዝገባውን ለመከልከል አዲሱ ሥም በማንኛውም ሁኔታ ቀደም ብሎ ከተመዘገበው ስም ጋር አንድዓይነት(identical) መሆን ይኖርበታል። ማለትም በሁለቱ ስሞች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር አይገባም።
- ሁለተኛው ጉዳይ ቀደም ብሎ የተመዘገበው ስም በሥራ ላይ ያለ ወይም በተለያዩ ምክንየቶች ያልተሰረዘ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።

የነጋዴው የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ የተመዘገበው የንግድ ስም መሰረዝ ይኖርበታል። ይህም ማለት አንድ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሥም ጋር አንድዓይነት መሆኑን ለመወሰን የምንመለከተው ሥራ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን የንግድ ስሞች ብቻ ነው።

በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰረዙ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ጋር የተያያዙ የንግድ ሥሞችን መመልከት አይኖርብንም።

**ለ. ቀደም ብለው ከተመዘገቡ ስሞች ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ያልሆነ**

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ተመዝግቦ በሥራ ላይ ካለ ሌላ የንግድ ስም ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይት ባይሆንም —ተመሳሳይና አሳሳች“ ሊሆን ይችላል። አዲሱ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሌላ የንግድ ሥም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ሆኖ ከተገኘ በንግድ ሥምነት ሊመዘገብ አይችልም።

ወደ ዝርዝር ከመግባቱ በፊት መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ የተከለከለው ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር —ተመሳሳይ“ ብቻ ሳይሆን —አሳሳችም“ መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት እንዲመዘገብ የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር —ተመሳሳይ“ በመሆኑ ብቻ ምዝገባ አይከለከልም። —ተመሳሳይ“ ቢሆንም —አሳሳች“ ሳይሆን ይችላልና።

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር —ተመሳሳይና አሳሳች“ (confusingly similar) የሚሆነው መቼነው? የሚለው ጥያቄ በንግድ ምዝገባ ሥርዓቱ ወሳኝ የሆነ ነገር ግን ቁርጥ ያለ መልስ ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ ነው። ጉዳዩ መወሰን የሚኖርበት የሚቀርቡትን ሥሞች በማወዳደር፣ በመመርመርና በማገናዘብ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ እንደሁኔታው (on a case -by- case- basis) ነው።

በአጠቃላይ ግን አንድ የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር —ተመሳሳይና አሳሳች“ ነው የሚባለው ሁለቱ ሥሞች ከመቀራረባቸው የተነሳ ሕብረተሰቡ አንዱን ሥም ከሌላው ጋር በማምታታት ሊሳሳት ይችላል ተብሎ ሲታመን ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ስም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር —ተመሳሳይ እና

አሳሳች“ መሆኑን ስመወሰን መጀመሪያ —ተመሳሳይ“ መሆኑን መወሰን ያስፈልጋል። —ተመሳሳይ“ መሆናቸው ከተወሰነ በኋላ ደግሞ —አሳሳች“ መሆናቸውም መወሰን ይኖርበታል።

እነዚህን ጉዳዮች ስመወሰን የተለያዩ ማነጻጸሪያዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል።

**ስምሳሌ፡-**

ሀ/ የሁለቱ ሥሞች ቃላት ቅርርብነት፣

ለ/ የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት፣

ሐ/ የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት እና

መ/ ሁለቱ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት ናቸው።

**ሀ. በሁለቱ ሥሞች ላይ የሚገኙት ቃላት ቅርርብነት**

አንድ ለምዝገባ የቀረበ ሥም ላይ የተጠቀሱት ቃላት ተመዝግቦ በሚገኝ ሌላ የንግድ ስም ላይ ከሚገኙ ቃላት ጋር አንድ ዓይነት ባይሆኑም እጅግ ተቀራራቢ በመሆናቸው አሳሳችሊሆኑ ይችላሉ።

- **ቀድሞ በተመዘገበ ሥም ላይ ቅጽሉችን መጨመር**

**ስምሳሌ ፡-** ሕብረት ቡና ንግድተብሎ የተመዘገበ የንግድ ስም ቢኖር፤

- የሕብረት ቡና ንግድ
- ሕብረት ቡና ንግድ ቁ. 2
- ሕብረት የቡና ንግድ
- የሕብረት የቡና ንግድ
- ሕ- ብ- ረ-ት ቡና ንግድ
- ሕብ-ረት ቡና ንግድ
- ሕብረቶች ቡና ንግድ ወዘተ ተመሳይና አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ነገርግንየአንድ ፊደልለውጥሁለቱን ስሞች ሙሉ በሙሉ ሊለውጥ ይችላል።

**ስምሳሌ፡-** —ጥረት የድለላ ሥራ“ እና —ጥራት የድለላ ሥራ“ ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ስሞች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ተመዝግቦ በሚገኝ ሥም ላይ ሌላ ሙሉ ቃል ቢጨመርበት ተመሳሳይና አሳሳች ሊባል አይችልም።

**ስምሳሌ፡-**እድገት በኅብረት ቡና ንግድ

ሕብረት ለሥራ ቡና ንግድ

ሕብረት ለእድገት ቡና ንግድ ወዘተ የሚሉ የንግድ ስሞች —ሕብረት ቡና ንግድ“ ተብሎ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ንግድ ስም ጋር —ተመሳሳይና አሳሳች“ ናቸው ማለት አይቻልም።

- **የቃላትን ቅደም ተከተል መቀያየር**

አንዳንድ ጊዜ ቀደም ብሎ የተመዘገበ ሥም ላይ የሚገኙ ቃላትን ቅደም ተከተል በመለዋወጥ የሚቀርብ የንግድ ስም ምዝገባ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ሥም ቀደም ሲል የተመዘገበውን የንግድ ሥም ቃላት በምን ያህል ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን በመቀያየር አሳሳች እንዳይሆን አድርጓል የሚለው መታየት ይኖርበታል።

**ለምሳሌ፡**—ሕብረት የቡናና ሻይ ንግድ— የሚል ቀደም ብሎ የተመዘገበ የንግድ ሥም ቢኖር እና "ሕብረት የሻይና ቡና ንግድ“ የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል መጠናኛና በአጠቃላይ በንግድ ስሙ ላይ ጎልቶ የወጣ ልዩነት የማያመጣ በመሆኑ —ተመሳሳይና አሳሳች“ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ በሁለቱ የንግድ ሥሞች መካከል የሚኖረው ልዩነት በግልፅ የሚታይ ሲሆን በሚችልበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ስም ቀድሞ ከነበረው የንግድ ስም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች አይደለም ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል።

**ለምሳሌ፡**-ሲስተም ኤሌክትሮኒክስ ንግድ እናኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ንግድተመሳሳይና አሳሳች ሳይባሉ ይችላሉ።

**የግለሰብ ስም የንግድ ስም ሆኖ መመዝገብ**

የግለሰብ ስሞች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ። ይሁንና ተመሳሳይ የግል ስሞች በመኖራቸው አንድ ነጋዴ ስሙን በንግድ ስምነት ካስመዘገበው ሌላ ነጋዴ የራሱ ስም ቢሆንም በንግድ ስምነት ለመጠቀም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ስም ጋር አንድ ዓይነት ነው ተብሎ ሊከለከል ይችላል።ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ በተቻለ መጠን ከተመዘገበው የንግድ ሥም ሊለይ የሚችለበትን ጭማሪ በማድረግ ለመመዝገብ መሞከር ያስፈልጋል።

**ለምሳሌ፡** —ወንድወሰን - የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ“ የሚል የተመዘገበ የንግድ ስምቢኖር ስሙ ወንድወሰን የሆነ ሌላ ነጋዴ ተመሳሳይ ስም ለተመሳሳይ የንግድ ሥራ ሊያስመዘግብ አይችልም። ይሁንና በስሙ ላይ ተጨማሪ ስም ወይም ቃል በመጨመር ሊመዘገብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

**ለምሳሌ፡-**

- ወንድወሰን ቶላ ጉርሜ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን ቶላ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን 8798 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድወዘተ የሚሉት የንግድ ስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስታወስ ያስፈልጋል። አንደኛ አንድ አይነት የግለሰብ ስሞች ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ አሳሳች ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው።

**ለምሳሌ፡** —ወንድወሰን የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ" የሚለው የንግድ ስም ቢኖርም —ወንድወሰን ፍራፍሬ ንግድ"፣ —ወንድወሰን ጨርቃጨርቅ ንግድ" ወዘተ የሚሉ የንግድስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

ሁለተኛው ፆታን ገላጭ ስሞች አንድዓይነት ስሞች ወይም —ተመሳሳይና አሳሳች" ሳይሆኑ ይችላሉ፡

**ለምሳሌ፡-**

- ታደሰ እና ታደሰች
- ዘነበ እና ዘነበች
- አበበ እና አበበች
- ተሾመ እና ተሾመች ወዘተ ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት ወይም —ተመሳሳይና አሳሳች" ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።

**ለ. የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት**

አንዳንድ ጊዜ ሊመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ሥም አፃፃፍ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር ልዩነት ቢኖረውም በአነባብ ግን —ተመሳሳይና አሳሳች" ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

**ለምሳሌ፡-**

- ኩልል የመጠጥ ውሃ እና ኩል የመጠጥ ውሃ
- Kool water እና Cool water
- Koka œkola እና Coka œ kola
- መጋቢት 15 ልብስ ስፌት እናመጋቢት አሥራ አምስት ልብስ ስፌትተመሳሳይና አሳሳች ስሞች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

**ሐ. የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት**

ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ሥም ቃላቶቹ ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር የተለያየ ቢሆንም ትርጉማቸው ግን አንድ አይነት ወይም የተቀራረበ ሊሆን ይችላል።

**ለምሳሌ፡-**

- አስተማማኝ ኮንስትራክሽን እናሪላይብል ኮንስትራክሽን
- ሉያል ትራንዚት እናታማኝ ትራንዚት

የእነዚህ ስሞች ትርጉሞቻቸው አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ቢሆኑም በራሳቸው ሲታዩግን ፈፅሞ የተለያዩ ናቸው። ኅብረተሰቡም ሁለቱን ስሞች ያምታታቸዋል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም እነዚህ ስሞች ሁል ጊዜ አሳሳች ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።

**መ. ሁለቱ የንግድ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት**

ሁለት የንግድ ስሞች ተመሳሳይና አሳሳች ሊሆኑ የሚችሉት የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች አንድ ዓይነት ወይም በጣም የተቀራረቡ ሲሆኑ ነው። ይህም ማለት አንድ ዓይነት የንግድ ስም ለተለያዩ የንግድ ዓይነቶች ሊሰጥ ይችላል።

**ለምሳሌ፡-** —ሞሐ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ“ የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- —ሞሐ የወፍጮ ንግድ ሥራ“
- —ሞሐ የልብስ ስፌት ሥራ“
- —ሞሐ ባልትና“ ወዘተ የንግድ ስሞችን መመዝገብ ይችላሉ።

በተመሣሣይ —አማኑኤል ፈለቀ ካፌ“ የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- —አማኑኤል ፈለቀ የእንጨት ሥራ“
- —አማኑኤል ፈለቀ ፋርማሲ“
- —አማኑኤል ፈለቀ የድለላ ሥራ“ ወዘተ የሚሉ የንግድ ሥሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

<u>ማጠቃለያ</u>

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር —ተመሳሳይና አሳሳች“ መሆን አለመሆኑ ሁለቱን ሥሞች ከላይ በተገለፁትና በሌሎች መመዘኛዎች በማወዳደር የሚወሰን ጉዳይ ነው። በተግባር የተለያዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ያሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰን ይኖርባቸዋል።

በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ)የንግድ ስሙ ቀደም ሲል ያልተመዘገበ ቢሆንም ሌሎች ነጋዴዎችን ወይም ኅብረተሰቡን የሚያሳስት አለመሆኑ

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ያልተመዘገበ ቢሆንም ሕብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። ሊያሳስት ይችላል ተብሎ ከታመነም በንግድ ሥምነት አይመዘገብም።

ሕብረተሰቡን ሊያሳስትባቸው ከሚችልበት ሁኔታዎች የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

1. በአዋጁ አንቀጽ 16ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው ስም ንግዱ ያላግባብ ከመንግሥትጋር ግንኙነት እንዳለው ሲያስመስል ከቻለ ላይመዘገብ ይችላል። መንግሥት የራሱን አስተዳደራዊ ተቋማት የሚሰይምበት ስሞች አሉ።

**ለምሳሌ፡-**

- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- መምሪያ
- ቢሮ
- ማዘጋጃ ቤት ወዘተ...

እነዚህ ስሞችን በንግድ ስምነት መጠቀም ኅብረተሰቡ ንግዱ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት አለው ብሎ እንዲያስብ ሲያደርገው ይችላል።

**ለምሳሌ፡-**

- ሠላም የማዳበሪያ አስመጭ ኮሚሽን
- ታታሪ የሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ቢሮ ወዘተ አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከመንግሥት አካላት ወይም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግሥት አካላት ወይም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የምዝገባው ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም።

ይሁንና ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ሁለት ጉዳዮችን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ ደረጃ መዝጋቢው ስሙ ከየትኛው የመንግሥት አካል ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ስም ጋር እንደሚመሳሰል ማሳየት አለበት። የመንግሥት አካላት የሚጠሩበት ሥሞች ተለይተው ታውቀው ለምዝገባ የቀረበው ሥም ከእነዚህ ሥሞች ጋር ያሳስታል ተብሎ መወሰን ይኖርበታል። በኢትዮጵያ የመንግሥት አካላት ሥሞች በተለያየ ጊዜ ሊለዋወጡ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የሚታወቁት ሥሞች የሚከተሉትን ያካትታል፤

- ሚኒስቴር
- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- ቦርድ
- ድርጅት

- የክልል መስተዳደር
- የክልል ቢሮ
- የዞን መስተዳደር
- የከተማ መስተዳድር
- ማዘጋጃ ቤትወዘተ…

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሥም በተመለከተ እያንዳንዱ የልማት ድርጅት የሚቋቋመው በሕግ እንደመሆኑ የልማት ድርጅቶችን ሥም ማወቅ የሚቻለው ከሚቋቋሙበት ሕግ ላይ ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ የተጠየቀውን የንግድ ስም ምዝገባ ለመከልከል ስሙ ከመንግሥት አካላት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አይጠበቅበትም። ይልቁንም ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግሥት አካላት ስም ወይም ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ አይመዘገብም። የዚህም ምክንያት ሕብረተሰቡ በስሞቹ ሊሳሳት ስለሚችል ነው። በመሆኑም ለምዝገባ የቀረበው ስም ከመንግሥት አካላት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት ካልሆነ ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ መወሰን አለበት።

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የሠራተኛ ማኅበር ወይም ሌላ አይነት ማኅበር ወይም የእርዳታ ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ) ጋር ተመሳሳይ ነው። ይኸውም ለመመዝገብ የቀረበው ስም ከፖለቲካ ፓርቲ ወይም ከሠራተኛ ማኅበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ሥሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ሕብረተሰቡ የንግድ ድርጅቱ ከፓርቲዎች ወይም ከሠራተኛ ማኅበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አለው ብለው እንዲያስቡ በማድረግ ሊያሳስቱት ይችላሉ የሚልነው። መዝጋቢው ይህንን ውሳኔ ለመወሰን የሚመለከተው ሥም ኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ስሞች ወይም ተመዝግበው የሚታወቁ የሠራተኛ ማኅበራትን ስሞች ወይም የዕርዳታ ድርጅቶችን ስሞች ነው።

**ለምሳሌ፡-** ―ፋኦ (FAO) የወተት ልማት ንግድ“ የሚል የንግድ ሥም ለምዝገባ ቢቀርብ ፋኦ (Food and Agricultural Organization) ከሚባለው ተቋም ስም ጋር ተመሳሳይ ነው ሊባል ይችላል።

**በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የታዋቂ ሰዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም**

የታዋቂ ሰዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገድብባቸው ሁለትዋነኛ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንደኛው ኅብረተሰቡ እንዳይሳሳት ለማድረግና ሁለተኛው ደግሞ የታዋቂ ሰዎችን ክብር ለመጠበቅ ሲባል ነው።

አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ስም በንግድ ስምነት በመጠቀም እነዚህ ሰዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ ያሳቸውን መልካም ዝና ያላግባብ ለመውሰድ ሲሞክር ይችላል። ኅብረተሰቡ የታዋቂ ሰዎችን ሥም የተጠቀመውንግድ ከታዋቂው ሰው ጋር ግንኙነት ይኖረዋል የሚል እምነት ሊያድርበት ይችላል።

**ለምሳሌ፡-** ሀይሌ ገብረስላሴ በሩጫው ዓለም እውቅናን ያተረፈ ሰው ነው። እንዲሁም ሀይሌ በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ላይ መሰማራቱ ይታወቃል።ኅብረተሰቡ ሀይሌን በሩጫ ብቻ ሳይሆን በንግድም ያውቀዋል። አንድ ነጋዴ —ሀይሌ ገብረሥላሴ ብረታብረት ንግድ“ የሚል የንግድ ሥም ቢጠቀም ኅብረተሰቡ ንግዱን ከሀይሌ ገብረ ስላሴ ጋር ሊያገናኘው ይችላል። በመሆኑም የንግድ ስሙን ለማስመዝገብ የኃይሌን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

የታዋቂ ሰዎች ሥሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገደብበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የታዋቂውን ሰው ክብር ለመጠበቅ ነው። አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎችን ስም በንግድ ስምነት መጠቀም የሚችለው ተገቢውን ፈቃድ ሲያገኝ ብቻነው። ይህ ድንጋጌ የሚያካትታቸው —የታዋቂ ሰዎችን“ እና —የሀገርመሪዎችን“ ሥሞች ነው። ይሁንና —ታዋቂ ሰዎች“ የሚለው የሀገር መሪዎችንም ያካትታል ምክንያቱም የሀገር መሪዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂ ስለሚሆኑ ነው።

ለዚህ ድንጋጌ ተፈፃመሚነት መመለስ የሚጋባቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ። የመጀመሪያው ጥያቄ ታዋቂ ሰዎች ወይም የሀገር መሪዎች እነማን ናቸው? የሚለው ነው። የሀገር መሪዎችን ስም በኢንተርኔትና መሰል ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ማወቅ ብዙም ሳያስቸግር ይችላል። የታዋቂ ሰዎችን ዝርዝር ግን ማግኘቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ውሳኔው እንደሁኔታው እየታየ የሚሰጥነው። ሰዎች ከሌሎች በተለየ መልኩ ታዋቂ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል። በፖለቲካ፣ በስፖርት፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ በሙዚቃ ወዘተ ሰዎች በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ታዋቂነትን ሲያገኙ ይችላሉ። እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ግን ስሙ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቅ ሰው ስም መሆን ይኖርበታል። በሌላ አገላለፅ ሰውየው በአማካኝ ኢትዮጵያዊ የሚታወቅ መሆን ይኖርበታል። ኔልሰን ማንዴላ፣ ባራክ ኦባማ፣ አበበ ቢቂላ፣ ጥላሁን ገሠሠ፣ ማይክል ጃክሰን፣ ወዘተ አማካኝ ንቃተ ሕሊና ላለው ኢትጵያዊ የሚታወቁ ሥዎች ናቸው። ታዋቂነቱም በሀገር ዐቀፍ ደረጃ መሆን ይኖርበታል።

ድንጋጌው በየአካባቢው የሚታወቁ ሰዎችን የሚያካትት ከሆነ ለአፈፃፀም እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም መካተት የሚኖርባቸው በብሔራዊ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ሥሞች መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ ቀነኒሳ በቀለ በብሔራዊ ደረጃ የሚታወቅ ሰው ነው። በአንድ ወረዳ ወይም ቀበሌ የሚታወቅን ሰው ሥም ድንጋጌው ማካተት የለበትም። በዚህ መሠረት እንደ ሁኔታው የሚለዩ ታዋቂ ሰዎች ሥምን ለንግድ ሥምነት ለመጠቀም —ተገቢ ፈቃድ“ መገኘት ይኖርበታል። ይህም ማለት ታዋቂው ሰው ሥሙ በንግድ ሥምነት እንዲያገለግል ግልፅ የሆነ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል። አመልካቹ የታዋቂ ሰው ሥም በንግድ ሥምነት ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘቱን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ ድንጋጌው በህይወት የሌሉ ታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎች ሥምን ያካትታል ወይስ በሕይወት ላሉት ብቻ የተወሰነው? የሚለው ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ታዋቂ ሰዎች በህይወት የሌሉ ከሆነ ከወራሾቻቸው ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠየቃል። ታዋቂ ሰዎች ወራሾች የሌሉ ከሆነ ግን

ሥሙን ያስ ፈቃድ ስመጠቀም ይቻላል።በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ የሆነ ድንጋጌ አልተቀመጠም። በመሆኑም ድንጋጌው የሚያገለግለው በህይወት ለሚኖሩ ታዋቂ ሰዎች ስም ነው ብሎ መደምደም ይቻላል።

**የሚመዘገበው ስም በኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ሥምነት ያልተመዘገበ ቢሆንም በሌሎች አገራት የሚታወቅ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ስሞች መካከል መሆን የለበትም**

ይህ ድንጋጌ የሚመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገቡ የተወሰኑ የንግድ ስሞችን ነው። ሁለት ዓይነት ሥሞችን የሚመለከት ነው። አንደኛው በሌሎች አገራት የሚታወቅ ስም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለው ሥም ነው።

በሌሎች ሀገራት ልምድ እንደሚታየው በአንድ ሀገር ሕግ መሠረት ያልተመዘገበ የንግድ ሥም ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት ያላቸው የንግድ ሥሞች ጥበቃ የሚደረግላቸው በሀገሮች መካከል በሚደረግ ሥምምነት መሠረት ነው። የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ ግን ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም በሌሎች ሀገራት የሚታወቁናዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የንግድ ስሞች ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆኑ ስሞች ይኖራሉ። ይሁንና እነዚህን ሥሞች ለማወቅ ቀላል ላይሆን ይችላል። ለምሳሌም አንድ የንግድ ስም በሩዋንዳ የታወቀ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህንን ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት ግልፅ አይደለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ያልተመዘገበ ነገር ግን በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆነ የንግድ ስም ጥበቃ የሚደረግለት በኢትዮጵያ የሚታወቅ ሲሆን ብቻነው። በኢትዮጵያ የማይታወቅ ከሆነ የማይመዘገብበት ምክንያት የለም። በኢትዮጵያ የሚታወቅ ሲባል ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል ማለት አይደለም። የንግድ ሥሙ በሚታወቅበት የንግድ ዓይነት ወይም ሴክተር ኢትዮጵያ ውስጥ መታወቅ ይኖርበታል። ለምሳሌ አክሰስ ባንክ በናይጀሪያ የታወቀ ስም ሲሆን በኢትዮጵያ የባንክ ሴክተርም የታወቀ ስም በመሆኑ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ የሚሸፍን ይሆናል።

በአለም ዓቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የንግድ ስሞችም አሉ። ኮካ- ኮላ፣ አፕል፣ ሶኒ፣ ማይክሮ ሶፍት፣ ስታርባክስ፣ ሒልተን ፣ ቶዮታ ወዘተ በሰፊው ከሚታወቁ የንግድ ስሞች ጥቂቶች ናቸው። እነዚህ ስሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ባይመዘገቡም በኢትዮጵያውያን ዘንድ በስፋት የሚታወቁ ስሞች ናቸው። እነዚህን ሥሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ማስመዝገብ የሚቻለው ስሙን ለማስመዝገብና ለመጠቀም ፈቃድ መሰጠቱን የሚያሳይ ማረጋገጫ ሲቀርብነው። የሚቀርበው ማረጋገጫ የተለየ ፎርማት ባይኖረውም በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል።

- የአመልካቹ መጠሪያ ስም ወካይ ሲሆን ወይም
- ከንግድ ማኅበራት አባላት ስም የተውጣጣ ከሆነ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ ሲሆን ነው።

አንዳንድ ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ትርጉም የማይሰጡ ይሆናሉ። በአዋጁ መሠረት ለንግድ ስምነት የቀረቡት ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ከሆነ ሊመዘገቡ ይችላሉ።

**ለምሳሌ**፡-ጉ.ተ ኢንተርኔት ካፌ (ጉና ተራራ)

- አ.ም ሉጅ (አርባ ምንጭ)
- ኪ.ም የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ (ኪዳነ ምህረት)
- መ.ፎ የመንፅር ሥራ (መልቲ ፎካል)
- መ.ታ ኮንስልተንሲ (መልቲ - ታለንት)

በተመሳሳይ መልኩ ለንግድ ስምነት የቀረበው ምህፃረ ቃል የአመልካቹ ስም ወካይ ከሆነም ሊመዘገብ ይችላል።

**ለምሳሌ፡**

- ሽምሱ ሁሴን የሚባል ነጋዴ ሽ.ሁ ፍራፍሬ ንግድ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል።
- ከበደ ማሞ ቶላ የሚባል ነጋዴ —ከ.ማ.ቶ የመኪና ኪራይ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል።

ከንግድ ማኅበራት አባላት ሥም የተውጣጣ ከሆነ ደግሞ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ ሲሆን ምህጻረ ቃሉ በንግድ ስምነት ሊመዘገብ ይችላል።

ለምሳሌ በላይ፣ ኪሮስ፣ ስንቅነሽ እና ሌንጮ የሚባሉ ሰዎች አንድ የንግድ ማኅበር ቢያቋቁሙ በ.ኪ.ስ.ሌ የሚል የንግድ ስም ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ነገሮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል። አንደኛው ድንጋጌው የሚመለከተው ምህፃረ ቃል ብቻ በንግድ ሥምነት ሲቀርብ ነው። ምህጻረ ቃሉ ከሌላ ቃላት ጋር ተጨምሮ ለንግድ ስምነት ሲቀርብ ይችላል። ለምሳሌ —ጉ.ማ.ኔ አዋሽ ቆዳ ሥራ" የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ጉ.ማ.ኔ የሚለውምህፃረ ቃል ትርጉም ቢኖረውም ባይኖረውም ወይም የባለቤቱን ስም ይወክል አይወክል ሊመዘገብ ይችላል።

ሁለተኛው ጉዳይ ምህፃረ ቃሉ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች ከሆነ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ከሆነ ወዘተበተዘረዘሩ ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ሳይመዘገብ ይችላል። ለምሳሌ ባምላኩ፣ ለማ እና ጌታሁን የተባሉ ሰዎች የስሞቻቸውን የመጀመሪያ ፊደል በመውሰድ —ባ.ለ.ጌ" የሚል የንግድ ስም ማስመዝገብ ቢፈልጉ ሥሙ ከመልካም ጠባይ ወይም ሥነ - ምግባር ተቃራኒ ነው ተብሎ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል።

**በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ) የንግድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን የለባቸውም**

ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ስም በተለያዩ ምክንያቶች ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ - ምግባር ተቃራኒ ሲሆን ይችላል። አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ እንደ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያዩ ይችላል። አንድ ማኅበረሰብ ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሚላቸው በሌላ ማኅበረሰብ በተመሳሳይ ሳይታዩ ይችላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ሊመጣ ይችላል።

**ለምሳሌ፡**

- አንድን ሀይማኖት የሚያንቋሽሽ ሥም፣
- አንድን ቋንቋ ብሔር /ብሔረሰብ የሚያንቋሽሽ ስም፣
- ስካርን፣ ሴሰኝነትን፣ አደንዛዥዕፅን፣ ወንጀልን የሚያበረታታ ስም
- የአንድን ሰው መልካም ዝና የሚያጎድፍ ስም
- የአንድ ፆታ የበታችነት የሚያመለክት ስም፣
- ጦርነትን፣ ብጥብጥን የሚያበረታታ
- ጥላቻን የሚያመላክት
- የሀገሪትን መልካም ስም የሚጎዳ ስም ወዘተ…

አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ)አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ሰነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆን በእያንዳንዱ ሁኔታ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በአሁኑ ዘመን ግልፅ በሆነ መልኩ ለመልካም ጠባይ ወይም ለስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ስሞች በጣም ውስን ሊሆኑ ቢችሉም ሙሉ በሙሉ የሉም ማለት ግን አይቻልም። ይህ በሚያጋጥምበት ወቅት እንደ አጠቃቀሙ ሁኔታ (context) መወሰን ይኖርበታል።

**ለምሳሌ፡-** —ፍለርት ባር“ (Flirt Bar) የሚለው የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። የእንግሊዘኛው ቃል —Flirt“ መቀራረብን፣ መፈላለግን፣ መነካካትን ወዘተ የሚያሳይ ነው። ቃሉን በቡና ቤት ደረጃ ስንመለከተው ፆታዊ መቀራረብ፣ መተሻሸት ወዘተ የሚደረግበት ቦታን ሊያመለክት በመቻሉ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

# አባሪ IV

# የድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መረጃ ማሰባሰቢያ ቼክ ሊስትና ቅጽ

# Annex IV

# Check list and form to collect information post Post Licens

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **የኢፌዲሪ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**<br>**FDRE Ministry of Trade and Regional integration** | ቅጽ01<br>Form 01 | |
| **የውጭ ድጎረ ፈቃድ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ሥራ ቼክ ሊስት ቅጽ** | | የተሰጠው ቁ. | |

1.የንግድ ድርጅቱ/ነጋዴው/ ስምና አድራሻ

1. Name and address of the bussines organization/Trader

1.1.የድርጅቱ/የነጋዴው/ ስም________________

1.1. Name of the bussines organization/Trader______________________________

1.2.የድርጅቱ ባለቤት/ኃላፊ/ ዜግነት___________

1.2. Nationality of the owner/heads of the bussines organization

1.3. አድራሻ፡-

1.3. address

ክልል_____ከተማ___ ክ/ከ______ወረዳ___ የቤ.ቁ______የስልክ ቁጥር__________

Region_________________ City _____________subcity_________________ woreda_____

___________ house No.____________________ phone N.____________________

2. የድርጅቱ/ነጋዴው/ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሁኔታ

2. trade license of the business organization/ Trader

2.1.የንግድ ፈቃድ ቁጥር ______________________

2.1. Trade license Number_____________________________________________________

2.2.የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር(ቲን ቁጥር)_____________

2.2. tax identification number (TIN)________________________________________

2.3. የንድ ሥራ ዘርፍ _____________________

2.3. bussines sector ____________________________________________________

2.4. የንግድ ሥራ መስክ____________________

2.4. Bussines field ____________________________________________________________

______

3. የድርጅቱ/ግለሰቡ ቦታ ይዞታ ባለቤት/የውል ማስረጃ

ሀ) አለው ለ) የለውም

3. business organization/ Trader possessory right owner/ contractual evidence

A)Have B) have note

4. ድርጅቱ/ግለሰቡ እየሰራ ያለው ባስመዘገበው አድራሻ

ሀ) ነው ለ) አይደለም

5) business organization/ Trader working at the place he registerd

A)Yes B) No

5. የንግድ ሥራ ፍቃድ እድሳት ሁኔታ

ሀ) ታድሷል ለ) አልታደሰም

5. Renawal of trade licence

A)Renewed B) Not renewed

5.1. የንግድ ፈቃዱ የታደሰበት ጊዜ______________

5.1. date of renewal of trade License________________________

6. ከተፈቀደለት ፈቃድ ውጪ የሚሸጠው/የሚሰጠው አገልግሎት

ሀ) አለ ለ) የለም

6. Sell/provide service out of activities He licenced

A) There is B) there is No

7. የድርጅቱ/ግለሰቡ የመረጃ አያያዝ ሁኔታ

7. Evidence handling of the business organization/ Trader

7.1 የሚሸጣቸው ዕቃዎች ከየት እንደተገዙ የሚገልፅ ደረሰኝ

ሀ) አለ ለ) የለም

7.1. Reciept showing from where he buy the objects he is selling

A) There is B) there is No

7.2. የሚሸጣቸው የዕቃዎች ዓይነት እና የዋጋ ዝርዝር ለተገልጋይ በሚታይ መልኩ

ሀ) ተለጥፏል ለ) አልተለጠፈም

7.2. Types of objets he is selling and their price details on visible places to the customer

A) B)

7.3.የሚሸጣቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ሕጋዊ ደረሰኝ

ሀ) ይሰጣል ለ) አይሰጥም

7.3. receipt for the Goods he is selling and services he is providing

11. Name and signatur of the inspector who did the inspection

| | Name | Signature |
|---|---|---|
| 1. | ______________________ | ___________ |
| 2. | ______________________ | ___________ |
| 3. | ______________________ | ___________ |
| 4. | ______________________ | ___________ |

12. ኢንስፔክሽን በተካሄደበት ወቅት የነበረው የንግድ ድርጅት ባለቤት/ኃላፊ/ተወካይ/ሠራተኛ

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1. | ______________________ | ___________ | ___________ |

12. Name of the owner/Head/Agent/employee of the bussines organization presented during inspection

| | Name | signature | date |
|---|---|---|---|
| 1. | ______________________ | ___________ | ___________ |